# የአማራ ህዝብ ትግል እንዴት ይመራ?



(የመነሻ ሃሳብ ሰነድ)

በመስከረም አበራ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም

# ይዘት


መግባቢያ....................................................................................i

1 የአማራ ህዝብ ትግል ስህተትን የማይፈቅድነው፦ ...................................ii

2 የአማራ ህዝብ ትግል ጊዜ የለውም፦ ...........................................................iii

3 የአማራ ህዝብ ትግል አዲስ ስልት መከተል አለበት፦ ..............................iv

የአማራ ህዝብ ትግል ወቅታዊ ሁኔታ.............................................................1

የአማራን ህዝብ ትግል ለመምራት ታማኝ ያልሆኑ ሀይሎች..............................5

1 የኢትዮጵያ ብሄርተኝነትን ፖለቲካ አራምዳለሁ የሚለው የፖለቲካ ጎራ፦.....6

2 ብአዴንና ውላጅ ድርጅቶቹ፦.................................................................10

3 አብን፦ ...................................................................................................13

መሪ ለማውጣት ሊጤኑ የሚገባቸው ነገሮች ..............................................14

የአማራ ህዝብ መሪዎች ሊኖሯቸው የሚገቡ ብቃቶች/ስብዕናዎች .....................21

1 የአማራ ህዝብ ትግል አስፈላጊ ያደርጉ ዋነኛ አእማዳትን በውል የተረዱ፦..23

2 የትግል ፍኖተ-ካርታና ትንታኔ በጽሁፍ ሰንደው ማቅረብ የሚችሉ ..........25

3 በድርድር መድረክ የአማራን ህዝብ ጥቅም ማስከበር የሚችሉ...................27

5 ከግልስብ ዕና ግንባታ፣ከእኔነት (ego centric) ስሜት የራቁ.....................29

6 የትግል ስነ-ምግባሮችን የተላበሱ .......................................................30

ጥሩ መሪዎች እነማን ናቸው..................................................................31

1 ትግሉን አስፈላጊ ያደረጉ ምክንያቶችን (causes) ጠንቅቆ ማወቅ .............33

2 የትግሉን አላማና ግብ መረዳት...............................................................35

3 የትግሉን እውነተኛ መሪዎች ማወቅ.......................................................35

4 ተመሪነት አንጻራዊ መሆኑን መረዳት.......................................................37

5 መሪዎችን በማክበርና በግለሰብ አምልኮ መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ.. 38

መቋጫ...................................................................................... 40

# መግባቢያ

በኢትዮጵያ የዘውግ ፖለቲካ የመንግስታዊ ስልጣን ማጠንጠኛ ከሆነበት ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የአማራ ህዝብ በማንነቱ ምክንያት የተቃጡ በርካታ በደሎችን እያስተናገደ ይገኛል።ይህ በደል በዓይነቱ፣ በስፋቱ፣ እና በአሰቃቂነቱ እየጨመረ የመሄድ ባህሪ ያለው ሆኖ ሳለ ይህንኑ የሚመጥን ትግል በአማራው ሊሂቅ በኩል ሳይደረግ ከሰላሳ ዘለግ ያሉ አመታት አልፈዋል። በመሆኑም የአማራ ህዝብ መከራ በመቃለል ፈንታ እየተባባሰና እየተወሳሰበ እንዲቀጥል ሆኖ በስተመጨረሻው የህዝቡ በህይወት የመኖር መብት ሳይቀር አጠያያቂ የሆነበት ምዕራፍ ላይ ተደርሷል።

ይህ እንዲሆን ያደረጉ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋንኛው ግን የአማራ ህዝብ የመንግስት ስልጣን በያዘው የዘውግ ፖለቲካ ጎራም ሆነ ይህን ስርዓት በሚቃወመው ጎራ ሁነኛ መሪ ማግኘት ያለመቻሉ ነው። ይህ የአማራ ህዝብ ለረዥም አመታት የቆየበት የሁነኛ መሪ እጦት ለአማራ-ጠሉ የፖለቲካ ጎራ መጽናኛው ብቻ ሳይሆን የስልጣኑ ማራዘሚያ ምቹ መደላድል ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በአንጻሩ የአማራ ህዝብ ትግል ዋንኛ እንከኑ የሆነውን መሪ የማውጣት ችግር መቅረፍ ከቻለ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአማራ ህዝብ ላይ የተቃጣውን ማንነት ተኮር በደል ማስቆም ብቻ ሳይሆን ወደ አደገኛ መንገድ እየነጎደ ያለውን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሀይል ሚዛንን በማስጠበቅ ሀገራዊ የፖለቲካ ፈውስ ማምጣት ይቻላል። ይህን ገቢራዊ ለማድረግ ግን የአማራ ህዝብ ትግል በትክክለኛ መርሆች ላይ ቆሞ እንዲራመድ መደረግ አለበት።

የአማራ ህዝብን ትግል ወደ ድል በር ለማቃረብ ሦስት ዋና ዋና ነገሮችን በማጤን የትግሉን ቅኝት በእነዚህ ሦስት መርሆዎች የተዋደደ ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህ ሦስት የትግል ቅኝት መርሆዎች እርስ በእርስ የሚተዛዘሉና ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ናቸው። ከእነዚህ የአማራ ህዝብ ትግል ሊቃኝባቸው ከሚገቡ መርሆዎች ቀዳሚው የአማራ ህዝብ ትግል ከዚህ በኋላ መሳሳትን የማይፈቅድ መሆኑን በመገንዘብ ትግሉን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማስኬድ የሚለው ነው። በሁለተኛነት የሚመጣው ትግሉ ጊዜ የሌለውና እጅግ አፋጣኝ በሆነ ሁኔታ መደረግ የሚገባው መሆኑ ነው። ሦስተኛው መርሆ ትግሉ ከዚህ ቀደም ባልተኬደበት አዲስ መንገድ የሚከወን መሆን አለበት። እነዚህ ሦስት መርሆዎች ለአማራ ህዝብ መከራ ማብቃት የሚታገሉ ሀይሎች ሁሉ ትግላቸውን ሊቃኙባቸው የሚገቡ የአማራ ህዝብ ወቅታዊ ትግል ቅኝቶች መሆን አለባቸው። እነዚህን ነጥቦች የአማራ ህዝብ ወቅታዊ ትግል መርሆች ለማድረግ እንዲቻል ነጥቦቹ ምን ማለት እንደሆኑ ዘርዘር አድርጎ ማስረዳት ያስፈልጋልና ወደዛው እንለፍ።

## 1,የአማራ ህዝብ ትግል ስህተትን የማይፈቅድ ነው፦

ይህ ነጥብ የትግል መርሆ ማድረግ ያሰፈለገው የአማራ ህዝብ ትግል ከዚህ ቀደም በበርካታ የስህተት አዙሪቶች ሲሽከረከር የኖረ በመሆኑ ነው። ትግሉን ድል እንዲርቀው ያደረገው ይህ የስህተት አዙሪት ከሚሽከረከርባቸው ዋንኛ የስህተት አምዶች ውስጥ ቀዳሚው በአማራ ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎችና በኢትዮጵያ አጠቃላይ የፖለቲካ ችግሮች መካከል ሚዛን የጠበቀ ትግል ከማድረግ ይልቅ የአማራን ህዝብ አንገብጋቢ ጥያቄዎች አዳፍኖ ኢትዮጵያን መታደግ የሚቻል ይመስል 'ኢትዮጵያን የማዳን እዳን' በአማራ ትከሻ ብቻ ለመሸከም የመሞከሩ ከንቱ ልፋት ውስጥ መግባቱ ነው። ከዚህ ስሁት እሳቤ የሚቀዳው ሌላው የስህተት አዙሪት አምድ አማራ-ጠሉ ስርዓት የኢትዮጵያን ስም በመጥራትና ሰንደቃላማዋን በማሳየት የአማራን ህዝብ ትግል ለማምከን የሚያደርገው አታላይ አካሄድን መረዳት አለመቻሉ ነው። ብርቱ የፖለቲካ ተዋናይ መሆንና የህዝቡን መብት ማስከበር አለመቻሉ ነው።

ሦስተኛው የስህተት እሽክርክሪት መንስኤ የአማራው ሊህቅ የራሱን ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች አንጥሮ አውጥቶ ሁሉም ለየዘውጉ ጥቅም በሚሟሟትበት የፖለቲካ አውድ ውስጥ ብርቱ የፖለቲካ ተዋናይ መሆንና የህዝቡን መብት ማስከበር አለመቻሉ ነው። አራተኛው ስህተት የአማራ ህዝብ ትግል ለሰርጎ ገቦች ምቹ የመሆን ነገር ነው ። እነዚህ ስህተቶች በወቅቱ እርምት ሳይሰጥ የኖረው የአማራ ህዝብ ትግል አሁን ላይ በደረሰበት ወሳኝ ምዕራፍ ወቅት እነዚህን ስህተቶች በፍጥነት አርሞ ድል የሚያስመዘግብበት እንጅ ያደሩ ስህተቶቹን የሚደግምበት ሆነ ሌላ ስህተት የሚሰራበት ወቅት አይደለም። የአማራ ህዝብ ትግል በስህተት አዙሪት ውስጥ የቆየባቸው ዘመናት መርዘማቸው ህዝቡን ለውርደት ሞት የዳረጉ በመሆናቸው ከዚህ በኋላ የሚደረግ ስህተት የሚመነዘረው በንጹሃን የህይወት ዋጋ በመሆኑ ስህተትን መፍቀድ የንጹሃንን ሞት መፍቀድ ነው የሚሆነው። ስለዚህ ነው የአማራ ህዝብ ትግል ስህተትን የሚፈቅድ መሆን የለበትምና በከፍተኛ ጥንቃቄ መመራት አለበት የሚለው የትግሉ መርህ እንዲሆን ያስፈለገው ።

2, የአማራ ህዝብ ትግል ጊዜ የለውም፦

በሀገራችን ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ እጅግ እየተጋጋመ በመጣው የዘውግ ፖለቲካ ውስጥ ከሞላ ጎደል ሁሉም የሀገራችን ዘውግ ሊሂቃን ከፍተኛ የዘውገኝነት ንቃት ላይ ደርሰው የየዘውጋቸውን ጥቅምና ፍላጎት ማስከበር ሲችሉ (ቢያንስ ሲሞክሩ) የአማራው ሊሂቅ ግን የዘውጉን ህዝብ ጥያቄዎች ማስመለስና መብት ማስከበር ቀርቶ የአማራ ህዝብ እንደ አንድ የኢትዮጵያ የዘውግ ማህበረሰብ ያሉትን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ነቅሶ ማውጣት እንኳን ሳይችል ሰላሳ አመታት በከንቱ አልፈዋል። በውጤቱም የአማራ ሊሂቅም ሀገራችን በተዘፈቀችበት የዘውግ ፖለቲካ ውስጥ እንደ ሁነኛ የፖለቲካ ተዋናይ ሳይቆጠር በርካታ አመታት አልፈዋል፤ እነዚህ አመታትም የአማራ ህዝብ ጠበቃ የሌለው፣ የዘውግ ፖለቲካው ፍርደኛ ተከሳሽ ሆኖ የሞት ቅጣት ሲቀጣ ኖሯል። ስለዚህ የአማራ ሊሂቅ አሁን ላይ የሚያደርገው ትግል ህዝቡን የሞት ፍርደኛ ያደረገውን ያለፈውን ረዥም የመኝታ ዘመን የሚያካክስ፣ አፋጣኝና ከስህተት የጸዳ ሊሆን ይገባዋል። በሌላ አባባል የአማራ ሊሂቅ ከቆየበት ረዥም የመፋዘዝ ዘመን የተነሳ አሁን ላይ ለመሳሳትም ሆነ ብዙ ስህተትን ለማረም የሚተርፍ ጊዜ የለውም።

### 3, የአማራ ህዝብ ትግል አዲስ ስልት መከተል አለበት፦

በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ከዚህ ቀደም የተደረጉ ትግሎች በበርካታ ስህተቶችና መደናገሮች የተተበተቡ በመሆናቸው ትግሉ ወደየትም ፈቀቅ ማለት አልቻለም። አሁን ላይ የሚደረገው ትግል ታዲያ እጅግ አንገብጋቢ የህልውና ጥያቄን ያነገበ በመሆኑ ቀደም ሲል ከተጓዘባቸው ድል-አልቦ መንገዶች በተለየና በተሻለ መንገድ መጓዝ ይኖርበታል። የአማራ ህዝብ ትግል አዲስ የትግል መንገድን መከተል አለበት የሚለው መርህ በርካታ ጭብጦችን በውስጡ ያመቀ ቢሆንም የዚህ ጽሁፍ ዋንኛ ትኩረት በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ያለው የመሪ እጦት ጉዳይ ስለሆነ ከዚሁ አኳያ ትግሉ አዲስ ስልት መከተል አለበት ሲባል ከዚህ ቀደም የአማራ-ጠሉ ጎራ መጽናኛ ሆኖ የኖረው “አማራ መሪ የለውም” የሚለው እውነትነት የማያጣው ትልቅ የችግር ቋጥኝ ማንከባለል መቻል ማለት ነው። የአማራ ህዝብ ትግል ሁነኛ መሪዎችን ማውጣት ከቻለ ከዚህ ቀደም ከኖረበት ድል-አልቦ ትግል ወጥቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ አመርቂ ውጤት ማምጣት ይችላል። ሁነኛ መሪዎችም ማውጣት የሚቻለው ደግሞ ለአማራ ህዝብ መከራ ማብቃት የሚታገሉ ሀይሎችን ሁሉ በማሰባሰብ ከስብስቡ ውስጥ ትግሉን ዳር ማድረስ የሚችሉት መሪዎችን በመለየት ነው። ይህን ማድረግ ከተቻለ ጠንካራ መሪዎች ብቻ ሳይሆን አዋቂ ተከታዮችንም ማፍራት ይቻላል። እዚህ ላይ በአዲስ ስልትነት የሚታየው እርምጃ የአማራ ሀይሎችን ማሰባሰብ የሚለው ነጥብ ነው። ምክንያቱም ከዚህ ቀደም የነበረው የአማራ ሊሂቃን ትግል በአላማ ዙሪያ መሰባሰብ ላይ ውስንነቶች ያሉት ብቻ ሳይሆን እርስ በእርስ የመራገጥ አደገኛ አዝማሚያ የማያጣው ነበር። ሌላው በአዲስ መልክ ሊጀመር የሚገባው አካሄድ የአማራ ህዝብ ትግል በፖለቲካ ፓርቲ ብቻ ይመራ የነበረበት አካሄድ ነው። ይህ አካሄድ የማያስኬድ መሆኑ ከአብን (አማራ ብሔራዊ ንቅናቄ) ፍጻሜ መረዳት ይቻላልና ከፓርቲዎች በተጨማሪ የአማራ ህዝብ ትግል በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ የሲቪክ ማህበረሰቦች ጋር በተቀናጀ ሁኔታ መመራት ይኖርበታል። መሪ የሚወጣውም ከሁሉም የአማራ ድርጅቶች ውስጥ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ የአማራን ህዝብ ትግል ውጤታማ ለማድረግ ትግሉ ከላይ ለማብራራት በተሞከሩት የትግል መርሆዎች ላይ መቃኘት ይኖርበታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ እነዚህን መርሆዎች መሬት ላይ ካለው የተጋጋመ የህዝብ የትግል መንፈስ ጋር አቀራኝቶ ውድ ዋጋ እየተከፈለበት ያለውን ትግል በጥሩ አጨራረስ ለድል የሚያበቁ ሁነኛ መሪዎች ሊኖሩ ያስፈልጋል። ትግሉ በሁነኛ መሪዎች እጅ እስካልተቀመጠ ድረስ የህዝብ መስዋትነት ብቻውን ትርጉም ያለው ነገር ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ትግሉን ትርጉም ያለው ቦታ ላይ የማሳረፍ ጉዳይ በትግሉ ሜዳ ላይ የሚገኙ የአማራ ሊሂቃን ሀላፊነት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ይህን ትልቅ ሃላፊነት የተሸከመው የአማራ ልሂቅም የወደቀበትን ታሪካዊ ሀላፊነት በመረዳት አሁን እየታየ ያለውን ጤናማ ያልሆነ የእኔ ልቅደም አይነት ጥሎ የማለፍ፣ አፍኖ የማውራት አልባሌ አካሄድን ትቶ የህዝብ ደም እየፈሰሰበት ያለውን ትግል ዳር የማድረሱን የባለ አዕምሮ መንገድ ሊከተል ይገባል። ይህ ጽሁፍ መጻፍ ያስፈለገውም በአሁኑ ወቅት በአማራው ሊሂቅ ዘንድ እየታየ ያለው ትግሉን የሚያበላሽ የመሽቀዳደም፣ ድል የመቀማማት አዝማሚያ አሳሳቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

ይህ ጽሁፍ በቀጣይ ገጾቹ አሁን በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ እየታየ ያለውን የድል ሽሚያ ወደ መተባበርና የጋራ ድል ማስመዝገብ ምዕራፍ ሊመሩ የሚችሉ መሪዎች ለማውጣት ሊረዱ የሚችሉ አቅጣጫዎችን ለመጠቆም ይሞክራል። ጽሁፉ በቀጥታ ወደ ዚህኛው አላማው ከመግባቱ በፊት የአማራ ህዝብ ትግል አሁን ባለበት የእድገት ደረጃ ላይ ወደ አመራርነት መምጣት የሌለባቸው የፖለቲካ ሃይሎችን ይጠቁማል። ቀጥሎም የአማራን ህዝብ ትግል መምራት የሚገባቸው ሀይሎች እነማን ናቸው? የሚለውን ለማመላከት ይሞክራል። በመቀጠልም ከመሪ እኩል ተመሪም ለትግል ስኬት አይነተኛ ሚና ስላለው መሪ ከተገኘ በኋላ ከተመሪው ህዝብ ምን ይጠበቃል? የሚለውን ከዳሰሰ በኋላ በማጠቃለያ ነጥቦች ጽሁፉ ይቋጫል።

ይህ ጽሁፍ ለአንባቢያን ሲቀርብ የአማራ ህዝብ ትግል በአሁን ወቅት ያለበትን የመሪ ክፍተት ችግር ለመቅረፍ የሚቻልበትን ውይይት ለማጫር እንጅ በጽሁፉ ላይ የቀረቡት ሀሳቦች ብቸኛ እውነቶች ናቸው ለማለት አይደለም። በጽሁፉ ላይ የተቀመጡ የውይይት ሀሳቦች የአንድ ሰው ሀሳቦች በመሆናቸው ብቸኛ እውነቶች ሊሆኑ ስለማይችሉ የጽሁፉ ፋይዳ የውይይት ሀሳቦችን በማጫር ተመሳሳይ ጽሁፎች ወደ ውይይት ሜዳው እንዲመጡ በር መክፈት ነው። አንባቢውም ይህን ጽሁፍ በሚያነብበት ወቅት ከግንዛቤ ሊያስገባው የሚገባው ነገር ቢኖር ይህ ጽሁፍ የተጻፈበት አውድ ተጨማሪ ማጣቀሻ ማካተት በማይቻልበት በህሊና እስር ቤት ውስጥ መሆኑን ነው።

መልካም ንባብ (በመስከረም አበራ)

# የአማራ ህዝብ ትግል ወቅታዊ ሁኔታ

አማራ-ጠሉ ስርዓት ከሦስት አስርት አመታት ዘለግ ላለ ጊዜ በአማራ ህዝብ ላይ ሲያደርስ የነበረውን ማንነት-ተኮር ሁለንተናዊ ጥቃት በሚያመረቃ መልኩ ታግሎ መመከቱ ሳይሳካለት የኖረው የአማራ ህዝብ በአሁኑ ወቅት ተስፋ ሰጭ የትግል ምዕራፍ ላይ ይገኛል። የአማራ ህዝብ ትግል አሁን የደረሰበት አበረታች ደረጃ ላይ እንዲደርስ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም እንደ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ያሉ የአማራ ሊሂቃን የህይወት ዋጋ ከፍለዋል። ሆኖም የእነዚህ ሊህቃን ትግል በሀገር ቤት ስልጣን በያዘው አማራ-ጠል አስተዳደር ዘንድም ሆነ በዲፕሎማቲክ ማህበርሰቡ ዘንድ ሞገስ ማግኘት ሳይችል ዘመናት አልፈዋል። ይህ የሆነበት ዋንኛ ምክንያት ከፕሮፌሰር አስራት ሰማዕትነት በኋላ ትግሉን ስራየ ብሎ ይዞ ዳር ማድረስ የሚችሉ ብቁ መሪዎች ማግኘት ባለመቻሉ ነው። ይህ የአማራ ሊሂቃንን ተቆራኝቶ የኖረው ስንፈተ-ፖለቲካ አሁን ላይ በመላው አማራ ዳር እስከዳር የተቀጣጠለውን የአማራ ፋኖ ትግል ግድ እንዲሆን አድርጓል።

የአማራ ህዝብ ትግል በአሁኑ ወቅት የደረሰበት ደረጃ ጸረ-አማራው ገዥ መደብ ጨርሶ ያልጠበቀውና ያልተዘጋጀበት አሁንም ድረስ ለማመን እየተቸገረበት ያለ ነገር እንደሆነ መረዳት አያዳግትም። ትግሉ አሁን ያለበት ምዕራፍ በገጠር፣ በከተማ፣ በዲያስፖራ፣ ያለውን አማራ ሁሉ በአንድ ላይ ያስለፈና በሚያጓጓ የትግል ምዕራፍ ላይ የሚገኝ ነው። በመሆኑም ለወትሮው ለአማራ ህዝብ አሰቃቂ እልቂትና ሁለንተናዊ ጥቃት ድፍን ጆሮ የነበራቸው ምዕራባዊያን፣ የሰብዓዊ መብት ተቋሞቻቸውና አህጉራዊ ህብረቶቻቸው ሁሉ ጆሯቸውን ወደ አማራ ህዝብ ትግል እንዲያዘነብሉ ሆኗል። ይህ በፍጥነት እየተመዘገበ ያለው ድል የአማራ ህዝብ መከራ፣ መጠቃትና መሳደድ ሲያሳስበው ለኖረው ሁሉ ትልቅ የምስራች መሆኑ አያከራክርም። ሆኖም የአንድ ህዝብ ትግል ሂደት ስኬታማ መሆን ለውጤታማነቱ ዋስትና ሊሆን ስለማይችል የትግሉ አጨራረስ ከትግሉ ሂደት እኩል ሊታሰብበት ይገባል።

የአማራ ህዝብ ትግል መፋፋምና በትግሉ አካሄድ ተስፋ መሰነቅ መልካም ነገር ቢሆንም የትግል ግብ ግን አይደለም። የትግሉ ዋንኛ ግብ የአማራን ህዝብ ሁለንተናዊ ጥቅሞች ማስከበርና ለዘመናት ሲረገጥ የኖረውን ሰብዓዊ ክብሩን ማስመለስ ነው። ይህን ቀዳሚ ግብ ማረጋገጥ ነፍሱን ለመስጠት የቆረጠ ጀግና ታጋይ ብቻ ሳይሆን አርቆ አሳቢ የፖለቲካ መሪም ይፈልጋል። ትግሉን ዳር ማድረስ የሚችል ሁነኛ የፖለቲካ መሪ ካልተገኘ በስተቀር አመርቂ ትግል ማድረግ ከመስዋትነት በቀር የሚያመጣው ነገር አይኖርም። በትግል ውስጥ መስዋትነት የማይቀር ነገር ቢሆንም መስዋትነት የፖለቲካ ትርፍ ማስገኘት ካልቻለ ህዝቡ ሁለት ጉዳት ይጎዳል። ስለሆነም ለመስዋትነት ወደ ኋላ ያላለው የአማራ ህዝብ ከመስዋትነቱ የፖለቲካ ትርፍ ማስገኘት የሚችሉ ሁነኛ መሪዎችን በአፋጣኝ ከትግሉ ማዋለድ ይኖርበታል። ይህን ገቢራዊ በማድረጉ ረገድ የአማራ ህዝብ ትግል ከስጋት የተዋጀ አይደለም።

እየተጋጋመና እየተፋፋመ የመጣው የአማራ ህዝብ ትግል ባልተጠበቀ ሁኔታ ተስፋ ሰጭ ድሎች እያስመዘገበ ቢሆንም ተግዳሮቶቹም በዚያው ልክ ናቸው። ከተግዳሮቶቹ አንዱ ትግሉ ያስመዘገበውን ድል ተከትሎ የሀይል ሚዛን በማየት በርካታ የፖለቲካ ሀይሎች በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ እጣ ፈንታ እንዲኖራቸው በመራወጥ ላይ መሆናቸው ነው። እነዚህ ሀይሎች የአማራን ህዝብ ለዛሬው መራር ትግል ያነሳሳው ፈርጀ-ብዙ በደል ሲፈጸምበት ጆሯቸውንም ቀልባቸውንም የነፈጉት ነበሩ። ከእነዚህ ሀይሎች ውስጥ አንዳንዶቹ በትውልድ አማሮች በመሆናቸው ደርሰው የአማራ ጉዳይ ያገባናል ሲሉ የሚከተላቸው ቢጠፋ እንኳን የሚያደናግሩት አላጡም። እነዚህ አካላት በአመዛኙ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት የፖለቲካ እምነት እናራምዳለን የሚሉ ግን በትውልድ አማሮች የሆኑ ናቸው። እነዚህ ከዚህ ቀደም የአማራን ህዝብ በተመለከተ ያራምዱት የነበረው አቋም የአማራው ህዝብ እየታገለው ካለው አማራ-ጠል ስርዓት እሳቤ የተለየ አልነበረም። በመሆኑም የዚህ ጎራ በአሁኑ ወቅት ወደ አማራ ህዝብ ትግል መጠጋጋት እጅግ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው አደገኛ ነገር ነው።

ሁለተኛው ተግዳሮት የብአዴን ማንሰራራት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በፌደራሉ መንግስት ሞግዚትነት ወደ ስልጣን ወጥቶ መዋቅር ለመዘርጋት እየሞከረ ያለው የአዲስ አሽከሮች ስብስብ የሆነው ብአዴን የአማራን ህዝብ ትግል የማሽነፍ ጉልበት ባይኖረውም የህዝቡን የድል ቀን በማራዝም ረገድ የሚጫወተው ሚና አይጠፋም፡፡ በሦስተኝነት የሚጠቀሰው ተግዳሮት የአማራ ህዝብ ወቅታዊ ትግል በህቡዕ የሚደረግ በመሆኑ በትግሉ ውስጥ አይነተኛ ሚና ያላቸው አካላት በጋህድ ከህዝብ ጋር ተገናኝተው ትግሉን መምራት አለመቻላቸው ነው፡፡ በዚህ ላይ መንግስት የሚያደርገው የጅምላ እስር ትግሉ የፖለቲካ መሪዎቹን እንዲያጣ አድርጓል፡፡ ይህ በመሆኑ በመሬት ላይ እንብዛም የጠነከረ እግር ያልተከሉ ሀይላት “ሆድ ሲያውቅ” በሆነ አሳሳች መንገድ ለህዝቡ አጉል ተስፋ በመስጠት እንዲጠመዱ ሆነዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ትግሉን ወደ ፊት በመምራቱ አካሄድ ላይ በመምከሩ ሊበረታ የሚገባው የአማራ ሊሂቅ የራሱን ጀግና እያሞካሸ ሌላውን በማብጠልጠሉ ትርፍ የማያስገኝ ተግባር ላይ የሚጠመድ ሆኗል፡፡ የአማራ ሊሂቅ ተሰባስቦ የመምከርና የመደማመጥ ፈለግ ያላዳበረ መሆኑ ጥቅም-አልቦ የመገፈታተር አካሄድ ቶሎ እንዳይገታ አድርጓል፡፡ በአማራ ህዝብ ትግል ጉዳይ ላይ እንሰራለን የሚሉ ሚዲያዎች ትግሉ የህቡዕ በመሆኑ የተለያዩ የትግሉን ቡድኖች አግኝተው አነጋግረው ለእውነታው የተጠጋ ነገር ለህዝቡ ማቅረብ ሲገባቸው የራሳቸውን ጀግና ቀድመው አዘጋጅተው ያንኑ በማደናነቅና ሌላውን በማጣጣል፣ በመዝለፍ ላይ መጠመዳቸው ብሎም የሌላውን ወገን ሀሳብ ለማስተናገድ እስከመቸገር መድረሳቸው ችግሩን አባብሶታል፡፡

አንድ ትግል ህቡዕከሆነ ጋዜጠኛም ሆነ ሰፊው ህዝብ እውነታውን በቀላሉ መረዳት እንደሚቸገር በመገንዘብ ጋዜጠኞች እነሱ ያመኑበትን ሀይል ከማሞገሱ ጎን ለጎን ያልደረሱበት ሌላ የትግል አንጓ ሊኖር እንደሚችል በመገመትና የተለያዩ ሀይሎችን ሀሳብ አንሸራሽሮ ታጋዮችን የማሰባሰብ ስራ ላይ ቢጠመዱ የተሻለ እንደሚሆን መጠቆሙ አሁንም የዘገየ የሚባል ነገር አይደለም፡፡ ሚዲያዎች ይህን ማድረግ ካልቻሉ የአማራ ህዝብ ትግል በገጠሙት ችግሮች ላይ ሌላ ችግር እያመጡ እንደሆነ ሊረዱ ይገባል፡፡

የአማራ ህዝብ ትግል በርካታ ባለድርሻዎች እጃቸውን ያያያዙበት እንጅ በአንድ ወይም ሁለት ግለሰቦችና ቡድኖች ትክሻ ላይ የቆመ አይደለም፡፡ ትግሉ ህቡዕ በመሆኑ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ወደ አደባባይ ላይወጡ ይችላሉ፡፡ ይህን ተረድቶ የተበታተኑ የትግል ቡድኖቹን በማሰባሰብ ወደ ተባበረ የትግል ምዕራፍ ማሳደግ የአማራ ህዝብ ትግል እንዲያሸንፍ የሚፈልጉ ሚዲያዎችና ታዋቂ ግለሰቦች ሀላፊነት ነው፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለና አሁን በተያዘው "እኔ የወደድኩት ብቻ መጉላት አለበት" የሚለው አካሄድ ትግሉን ከማምከንና አምባገነንነትን ከማማጥ የዘለለ ውጤት አይኖረውም፡፡ የአማራ ህዝብ በየፊናው የሚታገለው ደግሞ በተባበረ ክንድ ጭቆናን ለማስወገድ እንጅ አዲስ አምባገነንነት ፍለጋ አይደለም፡፡ ይህ ሊታሰብበትና በቶሎ እርምት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

የትግሉ ህቡዕ ተፈጥሮ ያመጣው የትግሉን ተዋናዮች በብዛታቸውና በአበርክቷቸው መጠን ለህዝቡ ይፋ ለማድረግ አለመቻል ከላይ የተጠቀሰው የሚዲያዎች የአንጋሽነት ዝንባሌ ጋር ተደምሮ የአማራ ህዝብ ትግል በመሪ ማዋለድ ከባድ ሽኩቻና መራኮት ውስጥ እንዲጠመድ አድርጓል፡፡ ይህ ሽኩቻ ሁሉም በየፊናው ጥሩ የመሰለውን በመደገፍና ሌላውን በመንቀፍ እስከመዘላለፍ ደርሷል፡፡ ወጥቶ የመዘላለፍን ዝቅታ ያልወደደው ሰፊው ህዝብም "የዚህ ትግል መሪ ማን ነው?" የሚል ግራ መጋባት ውስጥ እንዲከርም ሆኗል፡፡ ይህ አካሄድ ከትግሉ ህቡዕነትና ከመንግስት አፈና ጋር የሚተሳሰር ነገር ስለሆነ ለምን ተፈጠረ ማለት አይቻልም፡፡ሆኖም ከዚህ በኋላም መቀጠል የለበትም፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ጠረንጴዛው መምጣት ያለበት ለአማራው ህዝብ ትግል የተሰለፉ የተለያዩ ሀይሎች ወደ አንድነት መጥተው ተመካክረው፣ ሁሉም ለህዝብ ትግል ስኬት የሰነቀውን አቅርቦ የተሻለው ተወስዶ ከስብስቡ ውስጥ ሁነኛ መሪዎች የሚወጡበት መንገድ ማፈላለጉ ላይ ነው፡፡ ይህን በማድረግ ረገድ አሁንም ሚዲያዎች ግንባር ቀደም ሊሆኑ ይገባል፡፡

ይህን በማድረግ የአማራ ህዝብ ትግል በጠንካራ መሪዎች የሚመራበትን መፈለግ ካልተቻለ “የአማራ ህዝብ ትግል በእነማን ይመራ?” ለሚለው አንገብጋቢ ጥያቄ ሁነኛ መልስ ካልተገኘ አሁን ብቅ ብቅ እያለ ያለው ወንድምን ጥሎ የማለፍ የድል ሽሚያና ውዝግብ ውስጥ መገባቱ አይቀርም።

ይህ የእርስ በእርስ እርግጫና ውዝግብ በጊዜ እልባት ካልተሰጠው ተአምር በሚመስል ሁኔታ ተስፋ ሰጭ ምዕራፍ ላይ የደረሰውን የህዝብ ትግል በአጭር የሚቀጭ ብቻ ሳይሆን የአማራን ህዝብ መልሶ በአማራ-ጠሉ ስርዓት መንጋጋ ውስጥ የሚከት አደገኛ ውጤት ሊያመጣ ይችላል። ስለዚህ በትግሉ ውስጥ ሚና ያላቸውን አካላት አሰባስቦ ከውስጣቸው መሪዎችን የማውጣቱ ስራ ለነገ ሳይባል በአፋጣኝ ሊሰራበት ይገባል። የአማራን ህዝብ ትግል መምራት ያለባቸውን መሪዎች ለማዋለድ የሚደረገውን ጥረት አመች ለማድረግ ትግሉን መምራት የሌለባቸውን ሀይሎች ቀድሞ መለየት ይስፈልግል።

## የአማራን ህዝብ ትግል ለመምራት ታማኝ ያልሆኑ ሀይሎች

የሚታገልበት በቂ የትግል ምክንያት (cause) ያለው ህዝብ ታግሎ ድል እንደሚያደርግ በአፍሪካም ሆነ በአለም ላይ የተደረጉ የህዝብ ትግል ታሪኮች ያስረዳሉ። ይህ የሚሆነው ግን የትግል ምክንያት ያለው ህዝብ ሁነኛ መሪም ማግኘት ሲችል ነው። የአማራ ህዝብ በህይወት የመኖር መብትን ጨምሮ ሌሎች መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን የመነጠቅን ያህል ከበቂ በላይ የሆነ የትግል ምክንያት ይዞ ለረዥም ጊዜ ድል ማስመዝገብ የቻለ ትግል ማድረግ አልቻለም። ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ የአማራ ህዝብ ጥያቄ ይመለሳል ተብሎ የታሰበው ትክክለኛ ባልሆኑ የፖለቲካ ቡድኖች መሪነት ስለነበረ ነው። በሌላ አነጋገር ላለፉት ዘመናት የአማራ ህዝብ ትግል ይመራ የነበረው ለህዝቡ ትግል ታማኝ ባልሆኑ የፖለቲካ ሀይሎች መሪነት ነበር። በዚህም ምክንያት ድል ማስመዝገብ አልቻለም።

ከእነዚህ ለአማራ ህዝብ ትግል ታማኝ ያልሆኑ ሀይሎች የመጀመሪያው በዜግነት የፖለቲካ ዘይቤ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ፖለቲካን አራምዳለሁ የሚለው ጎራ ነው። ሁለተኛው በአማራ ክልል የመንግስት ስልጣን ይዞ ያለውና የኖረው፣ የአማራ-ጠሉ ስርዓት ረኸርም ዱላ ሆኖ የገዛ-ህዝብን ትግል በመቀጥቀጥ ላይ ያለው ብአዴንና ውላጅ ድርጅቶቹ ናቸው። በሦስተኝነት ደረጃ የሚመጣው አብን የተባለው ፓርቲ የላይኛው አመራር ነው። እነዚህ ሦስት ሀይሎች የአማራ ህዝብ ትግል መርተው ድል ማስመዝገብ እንደማይችሉ በተግባር ተፈትነው የታዩ ናቸው። እነዚህ ሀይሎች የአማራን ህዝብ ትግል መርተው ድል ማስመዝገብ ያልቻሉበት መሰረታዊ ምክንያት የአማራ ህዝብን ትግልና ጥያቄዎቹን በተመለከተ ያለባቸው የትንታኔ ችግር ነው።

እነዚህ ሀይሎች ያለባቸው የትንታኔ ችግር የሚመነጨው አውቆ ከመተኛት ሲሆን መጠነኛ የግንዛቤ እጥረትም የችግሩ መንስኤ ሊሆን ይችላል። የትንታኔ ችግሩ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ የሆነው እጅግ በጣም ጥቂት ቁጥር ያለው የዚህ ጎራ አባልና ደጋፊ የኂላ ኂላ ጎራውን በመልቀቅ የአማራን ህዝብ ትግል በመቀላቀል ላይ ይገኛል፤ አውቀው የተኙት ግን ፍርድ በመገምደላቸው ቀጥለዋል። አውቆ በመተኛት የአማራን ህዝብ ትግል በስሁት ሁኔታ ተንትኖ የተሳሳተ መፍትሄ ይዞ የሚንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ጎራው አባላት ከፍተኛ የቅንነት ችግርም እንዳለባቸው መረዳት ይቻላል። እነዚህ ስሁት ትንታኔ ከቅንነት ማጣት ጋር ደርበው የያዙ የዚህ ጎራ አባላት ለአማራው ህዝብ ትግል ድል እንደማያመጡ ከተግባራዊ ስራቸው የተረጋገጠ ሲሆን የህዝቡን ትግል የማደናቀፍ አደገኛ አዝማሚያ እንዳላቸው ግን በውል ግንዛቤ የተያዘበት አይመስልም። እነዚህ ሀይሎች ከአማራ ህዝብ ትግል መራቅ ያለባቸው ለምን እንደሆነ ከድርጅቶቹ አኳያ ዘርዘር አድርጎ ማየቱ ጠቃሚ ስለሆነ ወደ እዛው እንግባ።

1, የኢትዮጵያ ብሄርተኝነትን ፖከቲካ አራምዳከሁ የሚከው የፖከቲካ ጎራ፡-

ይህ ጎራ የአማራን ህዝብ ትግል በተመለከተ ስር የሰደደ የትንታኔና የቅንነት ችግር ያለበት ነው። በመሆኑም የህዝቡን ትግል በተመለከተ የሚያራምደው አቋም የአማራ ህዝብ ትግል ከቆመበት ዋንኛ አምድ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጋጭ ነው።

የአማራ ህዝብ ትግል ዋንኛ አምድ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በሀገራችን ስልጣን የያዘው ቡድን የአማራን ህዝብ በዘውጋዊ ማንነቱ ምክንያት የሚያጠቃ፣ የሚጨፈጭፍና የሚያሳድድ ነው:: በዚህም ምክንያት የአማራ ህዝብ የማንነት ተኮር ጥቃት ሰለባ ነው የሚል ነው:: የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ፖለቲካን አራምዳለሁ የሚለው ጎራ ደግሞ የአማራ ህዝብ በማንነቱ የተንሳ የደረሰበትም ሆነ የሚደርስበት ጥቃት የለም ሲል የሚታየውን ሀቅ በመካድ ፍርድ ይገመድላል:: በዚህ ክርክሩ ውስጥ አማራው በዘውግ ማንነቱ ምክንያት የመጣበትን ግልጽ ጥቃት ለመመከት በማንነት ተደራጅቶ መታገሉን አላስፈላጊ አድርጎ ከማየት እስከመቃወም የደረሰ አቋም አለው::

ግልጽ የሆነውን የአማራ ህዝብ ማንነት ተኮር ጥቃት የሚክደው ይህ ቡድን ይህንን አደገኛ አቋሙን እንደያዘም ቢሆን ለዘመናት የአማራን ህዝብ ቀልብ መሳብ ችሎ ኖሯል:: ለበርካታ አመታት የአማራን ሊሂቃንን በአባልነት፣ በደጋፊነት ና አንዳንዴም በመሪነት ይዞ ኖሯል:: በመሆኑም የዚህ ጎራ የፋይናንስና የቅቡልነት የጀርባ አጥንት የአማራ ህዝብ ሊሂቃን ሆነው ኖረዋል:: የአማራ ህዝብ/ሊሂቅ ከኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት ጋር ያለው ጥብቅ ትስስር ይሄን ጎራ በቅጡ ሳይመረምር አይኑን ጨፍኖ እንዲከተለው ብቻ ሳይሆን በገንዘብ በጉልበቱ እንዲሁም በህይወቱ ጭምር ሲያገለግለው እንዲኖር አድርጓል::

ለአማራ ህዝብ ትግል በጎ ነገር ሳይሰንቅም (በስሙ ላይ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ስለያዘ ብቻ) የአማራን ሊሂቅ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማግኘት የቻለው ይህ ጎራ የአማራ ህዝብ ትክክለኛ ትግል ይህን ከአማራ ሊሂቅ ሲሰበስብ የኖረውን ሁለንተናዊ ድጋፍ እንደሚያሳጣው ያውቃል:: ስለዚህ የአማራ ህዝብን ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች ነቅሶ አውጥቶ ለህዝቡ አርነት መውጣት የሚደረገውን የአማራ ህዝብ ትክክለኛ ትግል አምርሮ ይቃወማል:: ይህ ተቃውሞ የሚመነጨው ከአማራ ሊሂቅ መሰብሰብ የለመደውን የፋይናንስና ሌላ ድጋፍ ከማጣት ስጋት ብቻ አይደለም:: ይልቅስ ይህ ጎራ ስልጣን ከያዘው አማራ-ጠሉ ጎራ እኩል የአማራን ህዝብ ጨቋኝ፣ በዝባዥ፣ ትምክህተኛ፣ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር ዋንኛ ተጠያቂ ነው ብሎ ስለሚያስብ ጭምር ነው::

በዚህ ትንታኔው ምክንያት ይህ ኀይ ከአማራ ጠልነት አልፎ ሰሜን ጠልነት ድረስ የሚመነደግ በተግባር እንጅ በቃል የማይገልጸው አቋም አለው። በዚህ አቋሙ ምክንያት ከሰሜን ያልሆነን የፖለቲካ ሀይል አበክሮ ከመደገፍ አልፎ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መፍትሄ የሚመጣው ሀገሪቱን የሚመራው ሀይል ከሰሜን ወደ ደቡብ ሲወርድ ነው ብሎ ያስባል። ለዚህ ነው በትጥቅ ትግል ሳይቀር እታገለዋለው ሲለው ከነበረው ከህወሀት የባሰ የዘውገኝነት ዘይቤ ያለው የኦሮሞ ብልጽግና የሚመራውን መንግስት በካቢኔ አባልነት፣ በቦርድ አባልነትና በሌሎች ወሳኝ የስልጣን እርከኖች ላይ ተሰይሞ እያገለገለው የሚገኘው።

የኦሮሞ ብልጽግና መራሹ የዘውግ አስተዳደር በቁንጮ ስልጣኖች ላይ ተሰይሞ እያገለገለ ያለው ይህ ኀይ የአማራ ህዝብ በዘውጉ ተለይቶ በመጨፍጨፍ ላይ ስለመሆኑ መናገርና መታገልን ከዘረኝነት ቆጥሮ ያብጠለጥላል፣ "ሬሳ ቆጣሪ" ሲል ያጣጥላል። ከዚህም አልፎ የአማራ ህዝብ ትግል ከተፋፋመ ሀገር የማፍረስ አደጋ ይዞ ይመጣል ሲል ይፈርጃል። ይህ ኀይ የአማራን ህዝብ ትግል በተመለከተ ስር የሰደደ የትንታኔና የቅንነት ችግር አለበት የሚለው የዚህ ጽሁፍ ክርክር የሚመነጨው ከእነዚህ ነባራዊ ሀቆች ነው። የዜግነት ፖለቲካ አራማጅ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ፖለቲካ እመራለሁ እስካለ ድረስ በማንነቱ ምክንያት በየዕለቱ የሚሞተው የአማራ ህዝብም ኢትዮጵያዊ እስከሆነ ድረስ ይህን አንገብጋቢ የህዝብ ችግር የማታገያ አጀንዳ ማድረግ የሚጠበቅበት ነገር ነበር። በዚህ ላይ የአማራ ህዝብ /ሊሂቅ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ፖለቲካን በማራመድ በኩል ተስተካካይ የሌለው ጠንካራ ምርኩዝ መሆኑ ሲጨመርበት ይህ ኀይ በተግባር እያደረገ ያለው የአማራን ህዝብ ትግል የመካድ ሸፍጥ ምን ያክል አደገኛ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

የኢትዮጵያ ብሄርተኛ ነኝ የሚለው ይህ የፖለቲካ ሃይል በአማራ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን የዘር ጭፍጨፋ ከመካድ አልፎ አማራ የሚባል ህዝብ የለም እስከማለት ደርሶ የነበረ ቢሆንም አሁን የአማራ ህዝብ ትግል ብዙ መሰናክሎችን አልፎ ድል ማስመዝገብ ሲጀምር ያልተለመደ አቋም እያሳየ ይገኛል። ይህን አዲሱን አቋሙን የፋኖ ትግል መፋፋም ተከትሎ ባወጣቸው ተከታታይ መግለጫዎች አንጸባርቋል።

በእነዚህ መግለጫዎቹ የአማራን ህዝብ ለዚህ ትግል ያነሳሳው የደረሰበት በደል እንደሆነ በማውሳት ክዶት የነበረውን ነገር ለማመን ይዳዳዋል:: ሆኖም ይህ የድንገቴ ልውጥ አቋም ከልብ የሆነ እንዳልሆነ የሚስተው የለም:: ጎራው የአማራን ህዝብ ትክክለኛነት ለማመን ቢዳዳውም መግለጫውቹን እስከመጨረሻው መመርመር ለቻለ ግን በውስጡ የያዛቸው አደገኛ ሀሳቦች አሁንም ይህ ጎራ ለአማራ ህዝብ ትግል ከአማራ-ጠሉ ስልጣን የያዘ ጎራ የተለየ ማንነት እንደሌለው አመላካች ነው::ይህ ጎራ በግልጽ ከሚያወጣው መግለጫዎች ባሻገር ስለአማራ ህዝብ ትግል የሚሰጣቸው አስተያየቶች የትግሉን ደካማ ጎን ብቻ የሚያጎሉ፣ ጨለምተኛና አደናቃፊነት የማያጣቸው ናቸው:: ከእነዚህ እሳቤዎች ውስጥ ዋንኞቹ የአማራ ህዝብ ትግል ግብታዊ ነው፣ መሪ የለውም፣ መዳረሻ አላማውን አያውቅም፣ ኢትዮጵያን የማፍረስ አደጋ ያዘለ ነው፣ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ጎራውን በጠላትነት ፈርጆ በጥርጣሬ የሚያይ ነው፣ የሌሎች ብሄረሰቦችን ሊሂቃን ቅቡልነት ያላገኘ ነው የሚሉ ናቸው:: እነዚህ ጨለምተኛና ደካማ ጎን ፈላጊ አስተያየቶች ጎራው ለአማራ ህዝብ ትግል ካለው ስር የሰደደ የትንታኔ ችግር የሚመነጭ በመሆኑ ይህን ጎራ የአማራ ህዝብ ትግል አጋር አድርጎ ለመውሰድ እጅግ አዳጋች መሆኑ ታውቆ በየጊዜ የሚያነሳቸውን ተለዋዋጭ አቋሞች በጥንቃቄ መመርመር እንጅ እውነት አድርጎ መቁጠር ለተደጋጋሚ ስህተት የሚዳርግ ነገር ነው:: ሌላው በጥንቃቄ መታየት ያለበት ይህ ጎራ ይዞ የመጣው ተግዳሮት የጎራው አባል፣ አመራር፣ ደጋፊ የሆነው ከላይ የተዘረዘሩ ፖለቲካዊ ሸፍጦችን በአማራ ህዝብ ላይ የመፈጸሙን የፖለቲካ በደል፣ ሲያጋፍሩ የኖሩ የአማራ ተወላጅ ሊሂቃን ጎራው የደረሰበትን ኪሳራ ሲያዩ ወደ አማራ ህዝብ ትግል ያዘነበሉ መስለው ለመታየት እየሞከሩ መሆኑን ነው:: እነዚህ ግለሰቦች የአማራ ህዝብን ትግል የሚደግፉ የሚመስለውን ወቅታዊ አቋማቸውን በሚያንጸባርቁበት ጊዜ ያለፈ ጥፋታቸውን ጠብሰቅ አድርገው ከማመን ይልቅ የቀደመ ጥፋታቸውን ያሰሯቸው የአማራ ተወላጅ ያልሆኑ የጎራው መሪዎች እንደሆኑ አድርገው በማቅረብ ከተወቃሽነት ለማምለጥ ሲሞክሩ መታየታቸው ወደ አማራ ህዝብ ትግል መለስ ቀለስ የሚሉት የሀይል ሚዛን አይተው ይሁን በእውነት ለአማራ ህዝብ ትግል ለማዋጣት ይሁን የሚለው አጠራጣሪ ያደርገዋል::

እነዚህ ግለሰቦች የሚሉትን ከዚህ ቀደም በአማራ ህዝብ መከራ ላይ ፊት የማዞር ጭካኔ ላይ ያደረሳቸው የአንድ ወይንም የሁለት ሰው ተጽእኖ ነው የሚለውን አምነን ብንቀበል እንኳን ሌላ ጥያቄ ያስነሳል። ይኸውም ይህን ያህል በሰው ተጽዕኖ ስር የመውደቅ ፍቃደኝነት ያለው ሰው ለየትኛውም ትግል ትክክለኛ ሰው ሊሆን አለመቻሉ ነው። በመሆኑም እነዚህ ግለሰቦች ለአማራ ህዝብ ትግልም ሊታመኑ አይችሉም ማለት ነው። ይህ ሲባል ግን እነዚህ ሰዎች ስለ አማራ ህዝብ ትግል የተለወጠ አቋማችን ያሉትን በሚያንጸባርቁበት ጊዜ ይሰደቡ፣ ይብጠልጠሉ፣ ይዋረዱ ማለት አይደለም። ሊባል የተፈለገው እነዚህ ግለሰቦች ለአማራ ህዝብ ትግል ያላቸው አቋም ከቅንነት የመነጨና በእውነተኛ ጸጸት ላይ የተመሰረተ መሆኑን በተግባር እስከሚያረጋግጡ ድረስና የአማራ ህዝብ ትግል ጠንክሮ የማይቀለበስበት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ እነዚህ ሰዎች በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ወሳኝ ሚና በሚጫወቱበት ቦታ ላይ መቀመጥ የለባቸውም፤ እነሱም ይህን ማሰብ የለባቸውም ለማለት ነው።

2- ብአዴንና ውላጅ ድርጅቶቹ፦

ከኢህዴን ጀምሮ በተለየዩ ስሞች እየተጠራ ቢመጣም ግብሩ መታዘዝ ብቻ የሆነው ብአዴን የአማራን ህዝብ ትግል ሊመራ እንደማይችል የሚያከራክር ነገር አይደለም። ይህ ድርጅት ከተፈጠረ ጀምሮ በአማራ ላይ ሲሰራ የኖረውና እየሰራ ያለውን እንደ አለላ የቀላ ፖለቲካዊ ሀጢያት የሚያስተሰርይበት በቂ ጊዜ ተሰጥቶት ነበር። ድርጅቱ ግን በመታረም ፋንታ በማጥፋት እየባሰ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ስብስብ በዋንኛ የአማራ ህዝብ ትግል እጥፋቶች ላይ ( ማለትም የግዛትና የማንነት መብቶችን ማስከበር፣ ከዘር ማጥፋት/ማጽዳት ወንጀሎች ለመዳን በሚደረገው ትግል፣ “ለውጥ” የተባለውን ነገር ለማምጣት ባደረገው መዋጮ ልክ ትርጉም ያለው የፖለቲካ ስልጣን ተጋርቶ መብቶቹን ማስጠበቅን እውን በማድረግ ረገድ ወዘተ) ክህደት በመፈጸም የአማራ-ጠሉን ስርአት ጥቅሞችን በማገልገል ተጠምዶ የኖረ ነው። ብአዴን እነዚህን መሰልና ሌሎች ተጨማሪ የፖለቲካ ሀጢያቶችን እንዲሰራ ያደረገው የአፈጣጠር ችግር ስላለበት ነው።

ይህን ቡድን ፈጣሪው ህወሀት ሲፈጥረው የራሱን አካል እየበላ የሚወፍር የካንሰርነት ጠባይ ያለው አድርጎ ስለሆነ ከውልደት እስከ ሞቱ ይህን እያደረገ ይኖር ዘንድ ግድ ነው ።

የብአዴን ፈጣሪ ህወሀት ከመንበረ ስልጣን ሲወርድ ደግሞ ከህወሀት ተጠፍጥፎ በመሰራት ታናሹ ለሆነው ኦህዴድ/ኦሮሞ ብልጽግና ፈርሞ በአማራ ህዝብ ገላ ላይ ተለጥፎ የካንሰርነት ሚናውን አጠናክሮ ቀጥሏል። ለኦሮሞ ብልጽግና ለማደር ፈርሞ በአማራ ህዝብ ትክሻ ላይ ደግሞ ለመፈናጠጥ እየሞከረ ያለውን የብአዴንን አዲሱ ካቢኔ የሞሉት አዲስ ምልምሎች እንደቀደምቶቻቸው ሁሉ ራሳቸውን የናቁ ውስብስብ የፖለቲካ ጨዋታን ተረድቶ መጫወት ቀርቶ በቅጡ ዜና አዳምጠው የማያውቁ የሚመስሉ፣ እበላ ባይነትን ( opportunism) ብቻ ሰንቀው የመጡ የጠኔ ፖለቲከኞች፣ የአማራ ህዝብ በህይወት የመኖር መብቱን ለማስከበር የኢትዮጵያን ብሄር ብሄረሰቦችን ማስፈቀድ ያለበት የሚመስለው፣ ለየትኛው ጉዳይ ድርድር ለየትኛው ጉዳይ ትግል እንደሚያስፈልግ ለማወቅ እንደገና መወለድ ያለባቸው የሚመስሉ መሆናቸው በየሚዲያው እየቀረቡ ከሚዘባርቁት አሰልቺ ዲስኩር መረዳት ይቻላል።

እነዚህ የብአዴን ካድሬዎች አንድ ሰው እንዴት ፖለቲከኛ መሆን እንደሌለበት ለማስተማር የተቀመጡ የሚመስሉ መሆናቸው ጸሀይ የሞቀው ነገር ስለሆነ ብዙ የሚያነጋግረን መሆን የለበትም። አሁን ላይ ወደ ሀሳቡ ገበያ መግባት ያለበት ጠቃሚ ጉዳይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብአዴን ውስጥ እየታዩ ያሉ አዳዲስ ለውጦች መርምሮ ለአማራ ህዝብ ትግል እንዲጠቅሙ ማድረግ ነው።ከእነዚህ አዲስ ነገሮች የመጀመሪያው ከባለፈው አመት አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ የፓርቲው መካከለኛና የታችኛው የአመራር መዋቅር ባልተለመደ ሁኔታ የአማራን ህዝብ እውነተኛ ጥያቄዎች አንግቦ ኦሮሞ ብልጽግና መራሹን አስተዳደር በግልጽ መሞገት መጀምሩ ነው። የአማራ ህዝብ ትግል አሁን ለደረሰበት ደረጃ የዚህ መዋቅር አስተዋጽዖ አይጠፋበትምና ይህ አመራር ከላይኛው አመራር ተለይቶ መታየትና ላበረከተው አስተዋጽዖ እውቅና መስጠት አለበት። ይህን ማድረግ የአማራ ህዝብ ትግል አጋሮች በመጨመር ረገድ በጎ አስተዋጽዖ ያበረክታል።

በብአዴን ውስጥ ከታየው አዲስ እድገት ሁለተኛ ተደርጎ የሚወሰደው ለወትሮው የአማራ ህዝብ ትግል በመድፈቅ ይታወቁ የነበሩ ጥቂት የላይኛው አመራር አባላት ለህዝብ ትግል መጠነኝ ወገንተኝነት የማሳየት ዝንባሌ ማሳየታቸው ነው። ባልተለመደ ሁኔታ በፓርላማ ስለአማራ ህዝብ ጥያቄዎች መሞገታቸው፣የፋኖ ትግል መፋፋሙን ተከትሎ እናንተ ናችሁ ያደራጃችሁት  በሚል በብዛት ከስልጣን መወገዳቸው አንዳንዱቹን ወደ እስር ቤት መግባታቸው ለዚህ ለውጥ ፍንጭ ሰጭ ነው።እነዚህ አመራሮች ይህን አቋም እንዲይዙ ያደረጋቸው እውነተኛ ምክንያት ማወቅ አስቸጋሪ በመሆኑ የተለያዩ ግምቶች ይሰጣሉ። ከእነዚህ ውስጥ ይህን አቋም የሚያራምዱት የአማራ ህዝብ ትግል እያሸነፈ  ስለሆነ የሀይል ሚዛን አይተው አሰላለፋቸውን በማሳመር የድል አጥቢያ አርበኛ ለመሆን ነው ሲሉ የብአዴን መኳንንት ሳይቀር ይተቻሉ። ይህ እውነት ነው ቢባልና ብንቀበለው እንኳን የሀይል ሚዛን አይተው አሰላለፋቸውን ከህዝብ ጋር ማድረግ ያልቻሉ እስከ እለተሞታቸው የህዝብ ቁስል ላይ እንጨት ለመስደድ የማሉ ብዙ ብአዴናዊያን ስላሉ አቋማቸውን የቀየሩት የተሻሉ መሆናቸው ሊጤን ይገባል። በዚህ ሀሳብ መግባባት ከተቻለ ባለቀ ጊዜም ቢሆን የህዝብ ወገንተኝነት ፍንጭ ላሳዩ በጣም ጥቂት የላይኛው አመራሮችም እውቅና መስጠትና ለአማራ ህዝብ ትግል መሳካት የሚያዋጡት ነገር ካለም በሩን ዝግ አለማድረግ ያስፈልጋል።

ስለ ብአዴንና የአማራ ህዝብ ትግል መሪነት ጉዳይ ሲነሳ ሊታለፍ የማይገባውና በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ብአዴን ስለፈጠራቸው የሲቪክ ማህበራት እና የአማራ ባለሃብቶች ጉዳይ ነው። የአማራ ምሁራን መማክርት፣ የብአዴን ካድሬ ወጣቶች ማህበራት፣ እንደ ጥረት/አልማ አይነት ማህበራት ከእነዚህ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። ብአዴን ራሱ በቀጥታ የአማራን ህዝብ ለመምራት የማይችልበት ነገር ከተፈጠረ በድርድር ምክክር ስም እነዚህን ተቋማት አሰልፎ  ሁለተኛ የሚወለድበትን ቀዳዳ መፈለጉ አይቀርም። እነዚህ የሲቪክ ማህበራት ብአዴን በአምሳሉ የፈጠራቸው፣ የብአዴን የካንሰርነት ተፈጥሮ ያለው የፖለቲካ አንጎል ተውሰው የሚንቀሳቀሱ ነገር ግን ይህን ተፈጥሯቸውን በግልጽ የማያምኑ ናቸው።

አሁን ብዙ እየተወራለት ባለው ሃገራዊ ምክክር ላይ የአማራ ህዝብ ፖለቲካዊ ፍላጎት ይወክላሉ ተብለው በአማራ-ጠሉ ስርዓት እንደሚመረጡ ጥርጥር ያለው ነገር አይደለም። የአማራ ምሁራን መማክርት የሚባለው ማህበር አመራሮች ይህን አደገኛ ተልዕኮ ተቀብለው እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ መረጃው አለ። እነዚህ በአማራ ምሁራን ስም የሚንቀሳቀሱ የመማክርቱ አመራሮች በብአዴን አመራርነት ለመሰየም ወረፋ የያዙ የስልጣን አራራየሚያንቆራጥጣቸው ናቸው። የመማክርቱ አመራሮች እንዲህ ያለ አላማ ያላቸው ስዩመ-ብአዴኖች ቢሆኑም የመማክርቱ ማህበር ሰፊው አባል ግን የአማራ ህዝብ ትግል በውል ተረድቶ የበኩሉን ለማበርከት ቁጭት አዘል ዝግጁነት ያለው ነገር ግን በእነዚህ ስዩመ-ብአዴን አመራሮች ታፍኖ የተያዘ እንደሆነ ከሁለት አመት በፊት ደሴ ላይ በተደረገው የመማክርቱ ጉባኤ ተገኝቼ አስተውያለሁ። ሰፊው አባል እነዚህን አመራሮች ለመቀየር ያደረገው ጥረትም እንዳልተሳካ መረጃው አለ። ስለዚህ የመማክርቱን ሰፊ አባል ከአመራሩ መለየትና ለአማራ ህዝብ ሊያበረክተው የሚችለውን ትግል አስተዋጽዖ እንዲያበረክት በማድረጉ ላይ መታሰብ አለበት።

3 - ኢብን፦

አብን የተባለው ፓርቲ የአማራ ህዝብ ችግር ለመተንተን በመሞከር ከብአዴን የተሻለ ነገር ያለው ቢመስልም በተግባር በሚያደርጋቸው ድርጊቶች ግን እምብዛም ከብአዴን የተለየ ፓርቲ እንዳልሆነ በተግባራዊ ስራው አስመስክሯል። በስልጣን ላይ ካለው የአማራ-ጠል ስርዓት ጋር በፌደራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር የካቢኔ አባልነትና ሌሎች ስልጣናት በመሰየም ለመስራት በመፍቀዱ ዋናው ብአዴናዊ መልኩ ነው። በአማራ ህዝብ ላይ የሚደርሱ ዘር ማጥፋትን የመሰሉ በደሎችን በተመለከተ የላይኛው አመራር በሚያሳየው የምንግዴ አካሄድ ሳቢያ ከመካከለኛውና የታችኛው የአመራር መዋቅር፣ ከሰፊው አባል ጋር የገባበት ግጭት የመዋቅሮቹን ግንኙነት እስከመበጣጠስ መድረሱ፣ በስተመጨረሻም እንደ ብአዴን ሁሉ አብንም የላይኛው አመራር ብቻውን ተንጠልጥሎ ከአማራ-ጠሉ ስርዓት ጋር ህብረት ያደረገበት ሁኔታ ብአዴንን የሚመስልበት ሁለተኛው ተፈጥሮው ነው።

የአብን የላይኛው አመራር የአማራ ህዝብ ትግል በአውራጃዊነት፣ በወንዘኝነትና በመንደርተኝነት በመከፋፈል የአማራ ህዝብ በማንነቱ ሳቢያ የገጠሙትን አንገብጋቢ ፈተናዎች እንዳይጋፈጥ ጉልበቱን የማዛል ክህደት ውስጥ መግባቱ ከብአዴን ጋር የሚመሳሰልበት ሶስተኛው ባህሪው ነው። በእነዚህና ሌሎች እውነታዎች ሳቢያ አብን የአማራ ህዝብ ትግል መምራት እንደማይችል በሰፊው መግባባት ላይ የተደረሰበት ነገር ስለሆነ በዚህ ላይ ብዙ ጊዜ መጨረስ አያስፈልግም። ሆኖም የፓርቲው ዝቅተኛ/መካከለኛ አመራርና ሰፊው አባል እንዲሁም የአማራን ህዝብ ሸምጥጦ ባለመክዳት የተሻለ ነገር ያሳዩ የላይኛው አመራር ጥቂት አባላት በተለየ ሁኔታ ማየትና የትግሉ አጋዥ ሀይል መሆናቸውን ተረድቶ በትግሉ ሰፊ ማዕቀፍ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል።

## መሪ ከማውጣት ኪጤኑ የሚገባቸው ነገሮች

ስልጣን የያዘውም ያልያዘውም አማራ-ጠሉ የፖለቲካ ጎራ አማራው ተደራጅቶ የታገለ ቀን የቆመበት የፖለቲካ መሬት መቅለጥ እንደሚጀምርና ራቁቱን እንደሚቀር የተረዳ ነው። ይህ ቡድን አማራው ለአንድ አላማ ቆሞ መደራጀትና መናበብ ከቻለ ሊፈጥረው የሚችለው የፖለቲካ ጉልበት እጅግ ሀያል እንደሆነም እንዲሁ አሳምሮ ያውቃል። በመሆኑም አማራው እንዳይደራጅ በዘረኝነት እየወቀሰ ከማሳፈር ጀምሮ እስከማስገደድና መግደል የሚደርስ እርምጃ ሲወሰድ ኖሯል። አማራ-ጠሉ ጎራ አማራ በመደራጀቱና በመናበቡ ሊያጣው የሚችለውን የፖለቲካ ጉልበት የአማራው ሊሂቅ ከሚያውቀው በላይ ስለሚያውቀው አጥብቆ ይፈራዋል። ይህ የሚፈራው ነገር እንዳይመጣ ሌት ተቀን ሰርቶ አማራው እንዳይደራጅና እንዳይናበብ የማያሰናክሉ ስራው ሲሳካለት ኖሯል። ለዚህ የአማራ-ጠሉ ጎራ ስኬት በአማራው ሊሂቅ በኩል ያሉ ድክመቶችም አጋዥ ነበሩ።

ከእነዚህ የአማራው ልሂቅ ድክመቶች ዋንኛውበአማራው መደራጀት አስፈላጊነት አምኖ ወደ ትግል ሜዳ የገባው የአማራ ሊሂቅ የሚያደርገው ጤናማ ያልሆነ የእርስ በእርስ ውድድር ነው።

ይህ የእርስ በእርስ ውድድር መደማመጥና መከባበርን በመጠላለፍና መዘላለፍ ስለሚተካ ከልሂቃን ውስጥ የተሻለውን ቡድን ወደ መሪነት ለማምጣት አስቸጋሪ ይሆናል። ይህም ማለት በትግል ሜዳው የገባው ልሂቅ ጤናማ ባልሆነ ውድድር መንፈስ ውስጥ የሚገባ ከሆነ ሁሉም መሪ ለመሆን መራኮት ውስጥ ስለሚዘፈቅ የተወሰኑ ብቁ መሪዎችን ማውጣትም ሆነ መቀበል አስቸጋሪ ይሆናል።

ማንኛውም የህዝብ ትግል መሪዎችና ተመሪዎች አሉት። ሁሉም ሰው መሪ፣ ሁሉም ሰው ተመሪ ሊሆን አይችልም። ይህን መገንዘብ መሪ ለማግኘት የመጀመሪያው ወሳኝ ነገር ነው። ጥሩ መሪዎች ለማውጣት ጤናማ ያልሆነ ውድድርን አስወግዶ ተመሪ የመሆን ትህትና መላበስ ያስፈልጋል። ለትግል በቂ ምክንያት ያለው ሰፊው የአማራ ህዝብ የስልጣን ጥምና የጥቅመኝነት ተግዳሮቶችም አልፎ ትግሉን የሚመሩለት መሪዎች ቢያገኝ ለመመራት ዝግጁ እንደሆነ ብዙ ጊዜ በተግባር አሳይቷል። ህዝቡ ቁርጠኛ መሪዎች ከማጣቱ የተነሳ አንድ ሁለት ቀን በሚዲያ ብቅ ብሎ ስለ ብሶቱ የተናገረለትን ሊሂቅ ሁሉ መሪ ይሁነኝ ይሆን የሚል ተስፋ ይጥልበታል። እንዳለመታደል ሆኖ ግን የአድርባይነትን፣ የስልጣን ጥመኝነትን፣ ወላዋይነትን፣ እበላባይነትን ፣ ራስ-ወዳድነትና ከሁሉም በላይ ከሃዲነትን አስወግዶ የአማራን ህዝብ ትግል ዳር ለማድረስ የቻሉ ጽኑና ታማኝ መሪዎች ማግኘት ችግር ሆኖ ቀጥሏል። በዚህ ምክንያት አማራ-ጠሉ ጎራ “አማራ መሪ ስለሌለው ፍሬያማና ተገዳዳሪ ትግል ሊያደርግ አይችልም” እያለ ሲጽናና ኖሯል።

የተማረ የሰው ሀይል ያልቸገረው የአማራ ህዝብ መሪ ሊያጣ የቻለው እንዴት ነው? የሚለውን ወሳኝ ጥያቄ መጠየቅ ያስፈልጋል። ለዚህ ጥያቄ አማራ-ጠሉን ጎራ ብቻ ተጠያቂ ማድረግ የራስን ጥፋት ላለማየት መሸሽ ይሆናል። ለአማራ ህዝብ መከራ ማብቃት ለመታገል ወደ ትግል ሜዳ የወጡ አብዛኛዎቹ የአማራ ሊሂቃን እርስበርሳቸው የሚያደርጉት ጤናማ ያልሆነ ውድድርና መጠላለፍ የአማራን ህዝብ ትግል ዋንኛ አላማ እስከመርሳት የሚደርስበት ሁኔታ እንዳለ ካየሁት ተነስቼ መናገር እችላለሁ።

የወጡበት የአማራ ህዝብ የተጋረጠበትን የህልውና አደጋ የሚያክል ትልቅ ምስል አይተው በቅንነት ህዝባቸውን ለመታደግ ወደ ትግል ሜዳው የመጡ ቅን ሊሂቃን ወደ ትግሉ ከገቡ በኋላ ከገዛ የትግል አጋሮቻቸው የሚገጥማቸው ውድድርና ሽኩቻ፣ መጠላለፍና መጠፋፋት ተስፋ አስቆራጭ ነገር ውስጥ ይከታቸውና ከትግሉ የመሸሽ ጉዞ ይጀምራሉ። በዚህ ሳቢያ ለትግል በከፍተኛ ተነሳሽነት መጥቶ የነበረው የአማራ ሊህቅ በውስጥ ቁርቁስ ተሰላችቶና ተስፋ ቆርጦ ከትግሉ ሜዳ ለመውጣት ይገደዳል አልያም የህብረት ትግሉን ሸሽቶ ለብቻው በመብሰልሰልና በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ቁጭቱን በማስተንፈስ የትም የማይደርስ ድካም ይደክማል። ለዚህ ነው በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ጸንቶ ከሚቆይ ይልቅ ብቅ ብሎ የሚጠፋው የበረከተው። ስለዚህ ለአማራ ህዝብ መሪ ማጣት አማራ-ጠሉን ስርዓት ብቻ ተጠያቂ ማድረግን ትቶ ወደ ውስጥ ማየትና ቶሎ ራስን ማስተካከል ያስፈልጋል።

አሁን ያለንበት ጊዜ የአማራው ሊሂቅ የነበረበትን በየምክንያቱ የመቆራቆዝ፣ በየሰበቡ የመወዳደር ገንቢ ያልሆነ መንፈስ የምናሶወግድበትና የህዝብ ስቃይ በማስቆሚያው ዋናው ጉዳይ ላይ የምንመክርበት፣ ይህን በማድረጉ ረገድ የተሻሉ መሪዎችን አውጥተን በሚተልሙልን መንገድ ትግሉን ዳር ማድረስ የሚገባን ወቅት ነው። በዚህ ጽሁፍ መግባቢያ ክፍል ላይ እንደተገለጸው የአማራ ህዝብ ትግል ከቀደመ ልማዱ ወጥቶ ትግሉን በአዲስ መንገድ ማስኬድ አለበት። ካልሆነ በር ላይ የደረሰው የህዝብ ትግል ድል-አልቦ ልፋት ሆኖ ይቀራል ማለት ነው። የቀደመው ልክ ያልሆነ አካሄድ አሁን ላይ ለመተው የሚያስገድደን ዋናው ነገር የአማራ ህዝብ ትግል ዛሬ ላይ እያስከፈለ ያለው ዋጋ እንደቀደመው ጊዜ የጥቂቶች እስርና ሞት ብቻ አለመሆኑን ነው። አሁን ላይ ትግሉ በየቀኑ በአየር በምድር በሚወርድ እሳት እንደ ህዝብ እየተጠበስን ውድ ዋጋ የሚጠየቅበት የፍጻሜው ምእራፍ ላይ ደርሷል። ስለዚህ ትግሉ ወደ ቀደመው የእርስ በእርስ መጠላለፍና መሻኮት ለመመለስ መሞከር እሳት እየወረደ ባለው የተግባር ታጋይ ህዝብ ደም መቀለድ ይሆናል።

አሁን ያለንበት ጊዜ ተሰባስቦ፣ ተደማምጦ ፣ ከዋናው የትግሉ ግብ በመለስ ያለውን ማንኛውም ልዩነት አቻችሎ ሰፊው የአማራ ህዝብ በደሙ እየጻፈው ያለውን ትግል በፖለቲካዊ ድል መቋጨት ነው እንጅ መነታረኪያ፣ መጎሻሸሚያና በሁሉ ነገር መወዳደሪያ አይደለም። በዚህ ወሳኝ ወቅት የገዛ ወንድሙን ለማራከስ የሚሰየም ሁሉ ራሱን መግዛት ካልቻለ የትግሉ ባለቤት የሆነው የአማራ ህዝብ ታገስ ሊለውና ሊገስጸው ይገባል። ሰፊው የአማራ ህዝብ በጦር አረር እየተቃጠለ መታገሉ ሳይከብደው የጦር ወላፈን የማያገኘው ልሂቅ የራሱን የእበልጣለሁ ባይነት ስሜት መግታት ሊያቅተው አይገባም። ስለሆነም በገዛ ወንድሙ ላይ የሚከፈተው የስድብ ላንቃ ሊዘጋና በውይይትና ምክክር ሊተካ ይገባል።

በአሁኑ ወቅት ሁለመናው ተጋልጦበት የቀደመ አፈናውን ለማድረግ እየተቸገረ ያለው አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ህዝብ ትግል ላይ ከሚያመጣው አደጋ የበለጠ በአማራ ልሂቃን መካከል ያለው የእርስ በእርስ ሽኩቻ ትግሉን የመጉዳት አቅሙ ትልቅ ነውና ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ይህን አላስፈላጊ ንትርክ በማስቀም ረገድ ሰፊው የአማራ ህዝብ ትልቅ ሚና አለው። ለዚህ ቀላሉ መንገድ ወንድሙን ለመስደብ የሚመጣ ሁሉ ምኞት እንዳይሰማው ማድረግ ነው።  መሳደብ ፖለቲከኝነት እንዳልሆነ ሁሉን የሚያዳምጠው ህዝብ ሊናገር ይገባል። ማንም ግለሰብ ከትግል አላማ አይበልጥምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መገሰጽ ያለበት ሊገሰጽ ግድ ነው።

ለትግል የወጡ የአማራ ሊሂቃንን እንደ አንድ የእግር ኳስ ቡድን ብንወስዳቸው የቡድኑ አላማ ጎል አስቆጥሮ አሸንፎ መውጣት ነው። በዚህ ቀዳሚ አላማ ሁሉም ተጨዋቾች መስማማትና ለአላማው ስኬት መስራትይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ ግን “ጎልን ማስቆጠር ያለበኝ/ያለበት እኔ ወይም እኔ የምወደው ሰው ነው” ወደሚል ለጠላት ቡድን ብቻ ጠቃሚ ወደ ሆነ ዝቅታ መውረድ ይመጣል። በዚህ አይነት ለድል የማያበቃ እሳቤ ውስጥ ወደ ጫዋታ የገባ ተጫዋች የሚጋጠመው ከተገዳዳሪው ቡድን ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሱ ቡድን አባላት ጋርም ይሆናል ማለት ነው። በዚህ አይነት ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ድልን ማግኘት ቀርቶ ማሰብ ቂልነት ይሆናል።

የአማራ ህዝብ ድል እንዲያስመዘግብ ከተፈለገ ትግሉ እንዲህ ካለው እንዳይሆን የሆነ አካሄድ የጸዳ መሆን አለበት። ትግሉ እንዲህ ካለው ፍሬ-አልቦ ልፊያ ለመታደግ ከታች የተዘረዘሩ ነጥቦች በውል መጤን አለባቸው።

1- የአማራ ህዝብ ትግል ለበርካታ አመታት የተጠራቀሙ አያሌ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በርካታ ቁጥር ያላቸው መሪዎች የሚያስፈልጉት እንጂ በአንድ ወይንም ሁለት መሪዎች ጫንቃ ሊሞከር እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል። በአብዛኛው የአማራ ሊሂቃን ዘንድ የሚታየው የመሪነት ውድድር፣ መጠላለፍና እበልጣለሁ ባይነት መንስኤው ህዝቡ ያለበትን ፈርጀ ብዙ ችግር ካለመረዳት ትግሉ የሚፈልገው ውስን መሪዎችን ነው ብሎ ከማሰብ ነው። እንዲህ የሚያስቡ የአማራ ሊሂቃን ከራሳቸውና እነሱ ከሚወዷቸው ሰዎች ውጭ ያለ ሰው ሁሉ ወንበር የሚሻማ ተግዳሮት እንጅ አጋዥ መስሎ አይሰማቸውም። ሰከን ብሎ ማሰብ ከተቻለ ግን የአማራ ህዝብ ችግር ፖለቲካዊ ብቻ ስላልሆነ የሚፈለገው የፖለቲካ መሪዎችን ብቻ አይደለም። የአማራ ህዝብ በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ያለ ስለሆነ በኢኮኖሚው መስክ ተጨማሪ መሪዎች ያስፈልጉታል። በውትድርና በጸጥታና ደህነቱ መስክም እንዲሁ በርካታ መሪዎች ያስፈልጋሉ። ሀቁ ይህ ስለሆነ መሪ ማለት አንድ ሰው ወይም ውስን ታዋቂ ሰዎች ናቸው ብሎ የማሰቡ ጥራዝ-ነጠቅ አካሄድ ሊቀርና በየመስኩ በርካታ መሪዎች እንደሚያስፈልጉ መረዳት ያስፈልጋል። በሌላ አባባል አሁን ካሉ በጣም ጥቂት የአማራ ሊሂቃን ውስጥ አብዛኛውን በስድብ፣ በማጠልሸትና በማጣጣል ቀንሶ አንድ ወይንም የተወሰኑ ግለሰቦችን ለማንገስ የሚኬደው አካሄድ የአማራ ህዝብ ከሚፈልገው በርካታ ቁጥር ያላቸው ብቁ መሪዎች ፍላጎት ጋር የሚቃረን ነው። ይህ ማለት ያሉትን መሪዎች ቀርቶ ሌላ ተጨማሪ በርካታ መሪዎች ከብዙ አይነት ሀሳብና አመለካከት ጋር ሊመጡ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት።

ስለዚህ በጥቂት ሰዎች ራስ ተለክቶ የተሰፋው ዘውድ መሳይ ከንቱ ውዳሴ መቅረት ይገባዋል። የአማራ ህዝብ የሚታገለው ከተጋረጠበት የህልውና ስጋት ለመዳን እንጅ ማንንም ለማንገስ አይደለም። የአማራን ህዝብ ከህልውና ስጋት፣ ከፈርጀ ብዙ አንገብጋቢ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቹ ለመታደግ ደግሞ የበርካታ የአማራ ልሂቃን ተሳትፎ ግዴታ ነው።

ወደ ትግል ሜዳ ገብቶ አስተዋጽዖ ለማድረግ የሚያስፈልገው ነገር የአማራ ህዝብ በዘውግ ማንነቱ የተጋረጠበት የህልውና አደጋ መኖሩን መገንዘብና ይህን አደጋ ለመቀልበስ በማንነቱ ተደራጅቶ መታገሉ ምትክ የሌለው አማራጭ መሆኑን ከልብ አምኖ መቀበል ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሚያስፈልገው ጉዳይ ላመኑበት እውነት በምንም ሳይታለሉ መቆም መቻል ነው። ይህንን ያሟላና በቂ የፖለቲካ ግንዛቤ ያለው የአማራ ልሂቅ ሁሉ በቻለው አቅሙ ትግሉን ይመራ ዘንድ በሩ ክፍት መሆን አለበት። በአጠቃላይ የአማራ ህዝብ ትግል ስራው ብዙና ውስብስብ ሰራተኛው ግን ትንሽ ነው። ስለዚህ ተጨማሪ ሰራተኞች ወደ መሪነቱ ጠረንጴዛ እንዲመጡ የትግል ሜዳውን ሰላማዊና መስዕብ ያለው ማድረግ እንጂ በአስጨናቂ የመጠላለፍና የመጠፋፋት፣ የመዘላለፍና የመወራረፍ መንፈስ መሙላት አላዋቂነት ከመሆኑም ባሻገር በየጥጋጥጉ ደሙ ለሚፈሰው ንጹህ የአማራ ደሀ ህዝብ አለማሰብ ነው። አሁን የሚስተዋለው ጥቂቶችን የእግዜር ታናሽ፣ ለብቻቸው በቂና ሙሉ አድርጎ የማቅረቡ የአላዋቂነት አካሄድ በአማራ ህዝብ የድል መንገድ ላይ መቆም ነው። እንዲህ ያለው እሳቤ በእጅጉ ልንታገለው የሚገባ አደገኛ አዝማሚያ ነው።

የተወሰኑ አካላትን ለማንገስ የሚደረገው ሩጫ በሰዎቹ ተከልሎ የራስን ፍላጎት እውነትም መንገድም የሆነ ብቸኛ ንጥር-እውነት የሚያደርግ የአምባገነናዊ አስተዳደር ምስረታ ዋዜማ ነው። እንዲህ ያለው እሳቤ ስንታገለው ከኖርነው የህወሀት አስተሳሰብና አሁንም እየታገልነው ካለነው ኦሮሞ ብልጽግና መራሹ አስተዳደር እሳቤ ምን ይለየዋል? ደግሞስ ብአዴንን ለህዝብ አልታገለም ብለን ስናብጠለጥል በኖርንበት በዛው አንደበታችን እንደአቅማቸው ለህዝባቸው ሊታገሉ የወጡ ሰዎችን ምክንያት እየፈለጉ ማብጠልጠል የመናገር አምሮትን ከማስታገስ በቀር ምን ጥቅም ያመጣል?

2 - የአማራ ህዝብ ትግል አሁን የደረሰበት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ የደረሰው በበርካታ ታጋዮች ፊርጀ ብዙ የትግል መዋጮ መሆኑንመረዳት ያስፈልጋል። ይህን መረዳት ከተቻለ ለትግሉ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ መድረስ አስተዋጽዖ ያደረጉ አካላት ሁሉ በትግሉ የመሪነት ሚና ላይ መሳተፍ እንዳለባቸው ማወቁ አስቸጋሪ አይሆንም።

በተቃራኒው ለትግሉ አስተዋጽዖ ያደረጉ አካላትን በመሪነት አሳትፎ ፍላጎታቸውን ማካተት ካልተቻለ ትግሉ ድል ባገኘ ማግስት መገለል የተሰማቸው ታጋዮች ቅሬታ ለሌላ ትግል ሊያነሳሳቸው ይችላል። ይህ ደግሞ የሚፈለግ ነገር አይደለም። ከድል ማግስት የአማራ ህዝብ የሚያስፈልገው የከፋ ድህነቱን ለማሸነፍ በኢኮኖሚውና ማህበራዊ መስክ መጣጣር ነው እንጅ ክፍል ሁለት ግን አይደለም። አርቆ ማስተዋል፣ የራስን ስሜት ብቻ ከማዳመጥ ወጣ ብሎ የህዝብ ችግሮች ሰፋ ባለ መንገድ ማጤን የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። ስለዚህ መሪ የመሰየሙ ተግባር የበርካታ ሀይሎችን ይሁንታ ማግኘት የሚያስፈልገው፣ በወንድማማችነት/እህትማማችነት መንፈስ ተቀራርቦ ተመካክሮ የሚከወን ነገር እንጅ በስድብና ውረፋ የወደዱትን የሚያነግሱበት የጠሉትን የሚያሳድዱበት የአፈኞች ስልጣን እንዳልሆነ ሊጤን ይገባል።

3- ስልጣን ላይ ባለው አማራ-ጠል አስተዳደር አፋኝነት ሳቢያ በአሁኑ ወቅት የአማራ ህዝብ ትግል የህቡዕ መልክ እየያዘ መጥቷል። በዚህ ላይ ትግሉ በየአካባቢው ራሱን ባደራጀ ህዝብ የሚመራ በመሆኑ በርካታ ነገሮች ድብቅና ሚስጥራዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም ማንኛውም ተንታኝም ሆነ ጋዜጠኛ የሚያውቅ ከመሰለው ነገር ውጭ የሆኑ እውነታዎች ሊኖር ይችላሉ ብሎ ሁሉን ነገር በእርግጠኝነት ከመናገር መቆጠብና እውነታዎችን ከሌሎች ለማዳመጥ ፋታ መውሰድ የአማራን ህዝብ ትግል የሚያግዝ የብልህ ተግባር ነው። በተረፈ እውነትም መንገድም እኔ በማውቀው ልክ ብቻ ነው ማለቱ ትግሉን ወደ አደገኛ ገደል የመወርወር ያህል አደገኛ ነገር ነው። የህዝብ ትግል ፍሬ እንዲያፈራ እፈልጋለሁ የሚል አካል ማድረግ ያለበት ነገሮችን የማጣራት ትዕግስት ወስዶ መሬት ላይ እየተሰራ ያለውን ስራ በውል አጣርቶ ጥንካሬ ድክመቱን፣ መሬት የመርገጥ ጥንካሬውን ከነሰራተኞቹ ማወቅና ሁሉንም እንደ አቅሙ በስራው መጠን እውቅና መስጠት፣ ማበረታት ነው።

4 - የግልሰብ አምልኮ ተወግዶ በቡድናዊ የአመራር ዘይቤ (collective leadership) መምጣት ለትግሉ ዳር መድረስ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ህዝብን የድል ባለቤት ማድረግ እንዳይቻል ካደረጉ መጥፎ የፖለቲካችን ነቀርሳዎች አንዱ የግለሰብ አምልኮ ነው።

በእርግጥ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ ከሁሉ የበለጠ ዋጋ የከፈሉ፣ በአስደናቂ ጽናት ለህዝብ ትግል ራሳቸውን የሰጡ ጥቂት ግለሰቦች አሉ። እነዚህ ሰዎች መደነቅ መከበራቸው፣ ወደ መሪነት ጠረንጴዛ እንዲመጡ መፈለጉ የራሳቸው ጠንካራ ማንነት ያጎናጸፋቸው ክብር ነውና ትክክለኛ ነገር ነው። ጥፋት የሚሆነው ወደ ስልጣን የሚመጡት ብቻቸውን ሆኖ ተከታይ መሪዎች የመሰየሙ የማንገስ የማውረዱ ስራም ብቻቸውን ይስሩት የሚለው አካሄድ ነው። እነዚህን የትልቅ ስብዕና ባለቤት የሆኑ ሰዎችን ለአመራርነት ስናጭ ሊመሩ የሚመጡት ከሌሎች ወንድሞቻቸው/ እህቶቻቸው ጋር በተለይ ከእነሱ የተለየ እይታ ያላቸውን ሰዎችን ጨምረው በጋራ የአመራርነት መንፈስ መሆን አለበት። ሌላው ትልቅ ቁም ነገር ጥሩ መሪ ማለት ታዋቂ ሰው ብቻ አለመሆኑ ነው። ሳይታወቁ ግን ሁነኛ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ወንድም እህቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል። በተጨማሪም እኛ በጠንካራ ስብዕናቸው የምንወዳቸው ሰዎች ሰው ናቸውና ደካማ ጎን ሊኖራቸው እንደሚችልም ማሰብ ያስፈልጋል። ይህ ደካማ ጎናቸው የሚሞላው ደግሞ በሌሎች የትግል አጋሮቻቸው እንደሆነ ማጤን ከስህተት ያድናል። የደም ዋጋ እየከፈሉ ግን ታዋቂ ያልሆኑ ሰዎች እንዳሉ የፋኖ ትግል ግልጽ ማሳያ ነው። ስለዚህ የአማራን ህዝብ ትግል ለመምራት ታዋቂ የሆኑም ታዋቂ ያልሆኑም ግን ለትግሉ ውድ ዋጋ የከፈሉ ወገኖችም ሊካተቱበት እንደሚገባ ማወቅ አለብን። ትግሉ በታዋቂ ሰዎችና ጭፍሮቻቸው ብቻ ይመራ የሚባል ስህተት ውስጥ ከተገባ የትግሉ መደምደሚያ የህዝብን ሁለንተናዊ ጥቅም ማስከበር ሳይሆን የግለሰብን አምባገነንነት ማዋለድ ይሆናልና ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

## የአማራ ህዝብ መሪዎች ሊኖሯቸው የሚገቡ ብቃቶች/ስብዕናዎች

የአማራ ህዝብ ትግል በሁነኛ መሪ እጦት ሲንገላታ በመኖሩ ድል ማስመዝገብ እንዳልቻለ በቀደሙት ገጾች ላይ ለመግለጽ ተሞክሯል። በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ አሁን እየጎመራ ያለው የአማራ ህዝብ ትግል የቀደሙ ችግሮቹን መቅረፍ እንጅ መሳሳት እንደማይኖርበት በጥብቅ ተገልጿል።

ትግሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትክክለኛ ነገሮችን ብቻ እየሰራ መሄድ ያለብት ጊዜ የሌለው የህልውና ትግል መሆኑም እንዲሁ ሁሉንም የአማራ ታጋዮች ሊያግባባ እንደሚገባ መታወቅ አለበት፡፡ ይህን ሁሉ አሟልቶ ወደ ድል በር ሊያመራ የሚችል ትግልን እውን ለማድረግ ታዲያ ሁነኛ መሪዎች ከተጀመረው ተስፋ ሰጭ ትግል ውስጥ ማውጣት አማራጭ የሌለው ነገር ነው፡፡

የአማራ ህዝብ ትግል ሁነኛ መሪዎች እንደሚያስፈልጉት የሚያነጋግር አይደለም፡፡ በውል ተነጋግረንበት ወደ ተግባራዊነቱ ያልተሄደበት ነገር አማራ መሪዎች ያስፈልጉታል ከማለቱ አለፍ ብሎ የቀደመ ስህተትን ላለመድገም፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወሳኝ የፖለቲካ ድሎችን ለማስመዝገብ ያለ ስህተት የመጓዙን ትልቅ ሀላፊነት መውጣት የሚችሉ መሪዎች ምን አይነት ብቃትና ስብዕናን የተላበሱ መሆን አለባቸው የሚለውን ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በእጅጉ ሊያነጋግር ሲገባ እንደዋዛ ዝም ተብሎ የታለፈ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ወሳኝ የትግል ምዕራፍ በመደማመጥ፣ በመግባባትና ከስሜት በራቀ ልቦና ማለፍ ካልተቻለ ህዝብ ህይወቱን እየገበረበት ያለው የአማራ ህዝብ ትግል ድል ሊያስመዘግብ አይችልም፡፡ ይህን የሚፈልግ አማራ እንደማይኖር ግልጽ ነው፡፡ የማንፈልገው ነገር እንዳይመጣ ለማድረግ ታዲያ ግለሰቦችን ከመውደድ መጥላታችን ባለፈ የህዝብን ትግል እያሰብን፣ በሞት ጥላ ስር ለኖረው አሁንም በየተፈናቃይካምፖች ላለው ምስኪን ህዝብ እያሰብን መጓዝ ያስፈልጋል፡፡

መሬት ላይ ያለውን የሰፊውን የአማራ ህዝብ ችግር ማሰብ ከተቻለ ህዝቡ ያለበት እጅግ ዘግናኝ ችግር ከምንፈልገው (ከምንወደው) ጋር ብቻ ሳይሆን ከማንፈልገው (ከማንወደው) አካል ጋር ሁሉ ቁጭ ብለን ስለ ህዝብ ችግር ለመነጋገር ልቦና እናገኛለን፡፡ በመሰረቱ በዚህ ጽሁፍ ላይ በአማራ ህዝብ ትግል ታማኝ እንዳልሆኑ ለመግለጽ ከተሞከረው አካላት ውጭ ያለውን የአማራ ታጋይ የምንጠላበት ምክንያት ሊኖር አይገባም ነበር፡፡ የሆነ ሆኖ የሀሳብ ልዩነት፣ አለመግባባት የሰው ልጅ ባለበት ሁሉ ሊኖር ግድ ስለሆነይህ ለምን ተፈጠረ አይባልም፡፡

ነገር ግን ተቀራርቦ ተነጋግሮ ልዩነትን በማጥበብ በሞት ጥላ ስርና በተፈናቃዩ መጠለያ ጥላ ስር ያለውን ህዝብ ችግር መፍታት ቀዳሚ ያደረገ እርምጃ መውስድ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ የህዝብ ወገንተኝነትን ማስመስከር አይቻልም።

የህዝብ ችግር ግድ ብሎት ወደ ትግል የመጣ ግለሰብ፣ ድርጅት ሆነ ሚዲያ በአሁኑ ሰዓት ማድረግ ያለበት አንገብጋቢ ጉዳይ የአማራ ህዝብ ትግል በሁነኛ መሪዎች እጅ የሚገባበትን መንገድ በአስቸኳይ ማፈላለግ ነው። በዚህ ወሳኝ ምዕራፍ ስንጓዝ ለመሪነት የምናጫቸው ሰዎች ምንአይነት ብቃትና ስብዕና አጣምረው ቢይዙ ነው ብአዴንና አብን ከሰሩት ስህተት መዳን የሚቻለው የሚለውን ማጤን ያስፈልጋል። በመሆኑም የአማራ ህዝብ ትግል መሪዎች ሊሆኑ የሚበቁ መሪዎች ሊያሟሏቸው የሚገቧቸው ብቃትና ስብዕና ምን መምሰል አለበት የሚለውን ጉዳይ በተመለከተ ለውይይት መነሻ እንዲሆን ቀጥሎ ቀርቧል።

## 1 -የአማራ ህዝብ ትግል አስፈላጊ ያደረጉ ዋነኛ አእማዳት በውል የተረዱ፦

ከእነዚህ አእማዳት ቀዳሚው የአማራ-ጠሉ ጎራ ዋንኛ ባህሪያትን ጠንቅቆ መረዳት። ይህ ጎራ እጅግ አሳሳች፣ አደናጋሪና አታላይ ባህሪያትን በመጠቀም የአማራን ህዝብ ትግል ለመቀልበስ የሚሰራ ነው። እነዚህን ባህሪያት አለመረዳት ከዚህ ቀደም የመጡ የአማራ መሪዎች ዋነኛ ስህተት ነው። ይህን ስህተት የማይደግም መሪ አሁን ላይ ያስፈልጋል። ስህተቱን ላለመድገም ደግሞ የአማራ-ጠሉን ጎራ ማንነት በውል መገንዘብ ግድ ነው። ይህን የተገነዘቡ የአማራ ልሂቃን ዋና መለያ አማራ-ጠሉን ስርዓት በተመለከተ የማያወላውል አዝማሚያ የሚያሳዩና ጎራውን በመታገል ረገድ ወጥ አቋም ያሳዩ መሆን አለባቸው።

የአማራን ህዝብ ትግል  አስፈላጊ ያደረው ሁለተኛው የትግል አምድ የአማራ ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ለይቶ በመገንዘብ ከአጠቃላዩ ሀገራዊ የፖለቲካ ችግሮች ጋር ያለውን ትስስር ሚዛን ባስጠበቀ ሁኔታ ማስኬድ መቻል ነው።

በሌላ አነጋገር የአማራ ህዝብ ትግል ቀዳሚ አላማው የአማራ ህዝብ በዘውጋዊ ማንነቱ ብቻ የተጋረጠበትን የህልውና ስጋት በዘውጉ ተደራጅቶ መቀልበስ ነው። እንደ ሀገር ያለብንን ፖለቲካዊ ምስቅልቅል ለመፍታት በመጀመሪያ አማራው በህይወት መኖር አለበት። ቀጥሎም አማራው በሀገሩ ፖለቲካ ውስጥ ታሪካዊ ቦታውንና ግዝፈቱን በሚመጥን ደረጃ ወሳኝ ሚና የሚጫወትበትን ሁኔታ መፍጠር ነው። እነዚህን ድሎች ካስመዘገበ በኋላ የሀገራችንን የፖለቲካ ቀውስ ለመፍታት ከሌሎች የኢትዮጵያ ወንድም/እህት ህዝቦች ጋር በመምከር ለሁሉም የምትመች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ይሰራል። የአማራ ህዝብ ትግል ቅደም-ተከተል ይህን የሚመስል ሲሆን ነው የአማራን ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎችና ከነባራዊ ሀገራዊ የፖለቲካ ፈውስ የማምጣቱ ነገር ተመጣጣኝ የሚባለው። በአሁኑ ሰዓት የአማራን ህዝብ ትግል የሚመሩ መሪዎችን ስንሰይም ይህን የትግል ቅደም-ተከተልና የማመጣጠን ነገር በውል የተገነዘቡ መሆናቸውን እርግጠኛ መሆን አለብን።

ሦስተኛው የአማራ ህዝብ ትግል አምድ የአማራን ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች ጠንቅቆ ማወቅ ነው (እነዚህ ጥያቄዎች ለማብራራት ሌላ ሰነድ እያዘጋጀሁ እያለ እስር ስለቀደመኝ ለህዝብ ማድረስ አልቻልኩም። ሆኖም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የተብራራ ነገር ለማቅረብ የቻልኩትን ሁሉ አደርጋለሁ።) የአማራ ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች በርካታ ቢሆኑም በእኔ አረዳድ በሰፊው ለሁለት ከፍያቸዋለሁ። ይኸውም፦

1- የህልውና ጥያቄዎች

2- የፍትህ ርትዕ ጥያቄዎች

ይህ የአንድ ሰው አረዳድ ስለሆነ እንደ ሁኔታው ሊሰፋም ሊጠብም መቻሉ የሚጠበቅ ሆኖ የአማራን ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች ጠንቅቆ መረዳት ግን ትግሉን ከሚመሩ መሪዎች የሚጠበቅ ነገር ነው።

2 -የትግል ፍኖተ-ካርታና ትንታኔ በጽሁፍ ሰንደው ማቅረብ የሚችሉ

በሀገራችን የተሻለ ፖለቲካዊ ስርዓትን ለመፍጠር የተደረጉ ትግሎች ለድል ያልበቁበት ዋናው ምክንያት ትግሎቹ የተደረጉት ወይ ከሁነኛ ትንታኔ በፊት ነው፤አልያም እንደ 1968ቱ የህወሀት ማኒፌስቶ ባለስንኩል ትንታኔ ላይ ቆመው የተደረጉ ትግሎች በመሆናቸው ነው:: የባሰበት ደግሞ እንደ ደርግ ለደመወዝ ጭማሪ የታለመ የወታደር ትግል ስተት አድርጎ ቤተ-መንግስት እስከሚያስገባ ድረስ ያደረሰ ትግልና የታጋዩ መተላለፍ አባዜ ነው:: የሆነ ሆኖ የሀገራችን ፖለቲካ አድሮ-ቃሪያ ያደረገው የተከፈለው መስዋትነት አንሶ ሳይሆን መስዋት የሚከፈልለት ትግል ምክንያትና ግቦች በውል ተንትነው፣ በጽሁፍ ተሰንደው ለሰፊው ታጋይ/ህዝብ ከመድረሳቸውና በልቦና ከማደራቸው በፊት መስዋትነቱ መቅደሙ ነው:: የአማራ ህዝብ እንዲህ ካለው የፖለቲካ አዙሪታችን እንዲላቀቅ ከተፈለገ ይመሩናል ብለን ተስፋ የምናደርግባቸውን ወገኖች ለሰፊው ህዝብ የሚያቀርቡት የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ ይዘው ሊመጡ ያስፍልጋል:: ይህ ተጠባቂ የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ የአማራ ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች ከነባራዊ፣ ከሀገራዊ፣ ከቀጠናዊ፣ ከአህጉራዊ፣ ከመካከለኛው ምስራቅ፣ ከምዕራባዊያን/ምስራቃዊያን የፖለቲካዊ ሁኔታ አንጻር የተቃኙ፣ ጠላት የሚቀንስና ወዳጅ የሚያበዛ መንገድን በመከተል፣ የአማራ ህዝብ ትግል ለኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ቀጣይነትም ሆነ ቀደም ብለው ከተዘረዘሩ የፖለቲካ ሀይሎች ሁነኛ አጋር ሊሆን እንደሚችል አድርጎ ማቅረብ የሁነኛ መሪዎች ሃላፊነት ነው:: ስለሆነም ይመሩን ዘንድ የምናስባቸው ግለሰቦች ይህን የማድረግ ብቃት እንዳላቸው መመርመር ያሻል::

በተጨማሪም መሪዎቻችን እንዲሆኑ የምንሻቸው ወገኖች የሚያመጡት ትንታኔ የአማራ ህዝብ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ችግሮችን ሁሉ ተንትነው የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የማመንጨት አቅም ያላቸው መሆን አለባቸው::

በእነዚህና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትንታኔ ያቀረቡ መሪዎቻችንን በመቀጠል እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እየተደረገ ያለው ትግል የሚጓዙባቸውን ፍኖቶች ከጊዜ ርዝመትና ከትግል ስልት አንጻር ወዴት መሄድ እንዳለበት የሚያመላክት የትግል ፍኖተ-ካርታ ማቅረብ የሚችሉ ቢሆን ወደ ድል የሚደረገውን ጉዞ ያፋጥነዋል።

መሪዎቻችን የትግል ትንታኔና ፍኖተ-ካርታ እንዲያቀርቡ የምንጠይቅበት በሁለት አበይት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው ቀድሞ ትንታኔ መስራትና ትግሉ የሚሄድበትን ፍኖት ማወቅ ትግል እንዲሰምር የሚያደርግ ዋነኛው ጉዳይ በመሆኑ ነው። በተቃራኒው ያለሁነኛ ትንታኔና ፍኖተ-ካርታ የሚደረግ ትግል ወደ ባሰ ችግር ሊከት እንደሚችል ከተግባራዊ የፖለቲካ ታሪካችን የተረዳነው ነው። የ1960ዎች ትውልድ ድል-አልቦ ትግል፣ የህወሀት የ17 ዓመት ትግል አሁንም የብልጽግናአስፈሪ ጉዞ የዚህ ታሪካችን ምሉዕ ምስሎች ናቸው። እነዚህ ታሪካዊ ስህተቶች ላለመድገም መሪዎች የሁኔታ ትንታኔያቸውን ይዘው መገኘት አለባቸው። ትንታኔ ያደርጉ ዘንድ ከመሪዎቻችን የምንጠብቅበት ሁለተኛው ምክንያት ለትግል ያላቸውን መሰጠት፣ መረዳትና ቁርጠኝነት የምንለካበት ስለሆነ ነው። በዚህ ቅደመ ሁኔታ መሪዎቻችንን የምንለካ ከሆነ አላማ ያለውን ከሌለው፣ የድንገቴ-ታጋዩን ከሁነኛው ለመለየት ያስችለናል። እና እንደተመሪ እንዲህ ያሉ መረዳትን፣ መሰጠትንና ቁርጠኝነትን የሚጠይቁ ቅድመሁኔታዎችን ለመሪዎቻችን እንዲያሟሉ የምንጠብቅና የምንጠይቅ ከሆነ ወደ አመራርነት ከተመጣ በኋላ የሚኖሩ ክህደቶችና ሌሎች አላስፈላጊ ድርጊቶችን መቀነስ ይቻላል። እግረ-መንገዳችንንም መሪነት ስክነት፣ ብቃትን፣ መሰጠትንና ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ እንጅ በተንደርደር መጥተው የሚፈናጠጡበት ቀላል ነገር እንዳልሆነ ማስገንዘብ እንችላለን። ከሁሉም በላይ ትግላችን በገዛ መሪዎቹ እንዳይኮላሽ ማድረግ እንችላለን።

የትግል ሁኔታ ትንታኔና ፍኖተ-ካርታ በመሪዎች ይቅረብ ሲባል የአማራ ህዝብ ትግልን በአሁኑ ወቅት እየመሩ ያሉ ተዋንያን ብዙ ስለሆኑ በቁጥር በርከት ያሉ ትንታኔዎችና ፍኖተ ካርታዎች እንዲቀርቡ ይጠበቃል።

ግን የትና ማን ባመቻቸው መድረክ ነው የሚቀርቡት የሚለው ጥያቄ እንደሚመጣ እሙን ነው። ይህን የማድረጉ ሀላፊነት በአማራ ህዝብ ትግል ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሚዲያዎችና የአማራ ምሁራን ነው። ይህን የሚያደረግ የአማራ ታማኝ ምሁራን፣ ታላላቅ ግለሰቦች ያሉበት ቡድን መቋቋም አለበት። የአማራ ህዝብ ትግል በብዙ የተበጣጠሱ ተዋንያን መመራቱ የሚያሳስባቸው በርካታ የአማራ ምሁራንና ታላላቅ ግለሰቦች እንዳሉ እሙን ነው። እነዚህ ሰዎች እርስ በእርስ ተፈላልገው፣ የአማራ ታጋዮችን አፈላልገው ለትግሉ ዳር መድረስ የሰነቁትን የሁኔታ ትንታኔና ግብ ለእነሱ አይነት ታጋዮች አቅርበው በመጨረሻ የሁሉንም ትንታኔ ጨምቆ የያዘ የትግል ትንታኔና የትግሉ መሪዎች ማዋለድ ይቻላል። ይህ የሚሆነው ታዲያ ሁሉም ታጋዩ አስፈላጊ ነው፣ ረዳት ወንድም ነው ብሎ ማሰብ ሲቻል ብቻ ነው። በአማራ ህዝብ ትግል ላይ የሚሰሩ ሚዲያዎች በተለይ ይህን ልቦና ሊላበሱ ያስፈልጋል።ሚዲያዎቹ እዚህ ከፍታ ላይ መድረስ ከቻሉ የተለያዩ የአማራ ህዝብ ትግል ተዋንያንን በማሰባሰብ የማወያየቱንና ወደ አንድነት የማምጣቱን መድረክ ለምሁራኑና ታዋቂ ግለሰቦች ቡድን ማመቻቸት ይችላሉ። ይህን ማደረግ ከተቻለ ብቻ ነው የህዝባችን ትግል ድል ማስመዝገብ የሚችለው።

## 3 - በድርድር መድረክ የአማራን ህዝብ ጥቅም ማስከበር የሚችሉ

የአማራ ህዝብ ትግል የሚቋጨው በፖለቲካዊ ድርድር መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለም። ድርድሩ በዋናነት ስልጣን ከያዘው አማራ-ጠል ስርዓት ጋር ቢሆንም ትግሉ ዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ማህበረሰብን፣ እንደ አሜሪካና አውሮፓ/አፍሪካ ህብረት ያሉ ወሳኝ ቡድኖችንም ከአደራዳሪነት እስከ ታዛቢነት ሊያሳትፍ ይችላል። የአማራ ህዝብ ትግል እንዲመሩ የሚታጩ መሪዎች ታዲያ እንደዚህ ባሉ መድረኮች የአማራን ህዝብ ጥቅም ማስከበር የሚችል የፖለቲካ ድርድር የማድረግ ልምዱና ብቃቱ ሊኖራቸው ይገባል። እንዲህ ያለ ስኬታማ ድርድር ለማድረግ በተራ ቁጥር አንድ እና ሁለት ላይ የተጠቀሱት ብቃቶች አስፈላጊ ናቸው።

ይህም ማለት የህዝቡን ጥቅም የሚያስከብር ድርድር ለማድረግ የአማራን ህዝብ ጥያቄዎች ጥርት ባለ ሁኔታ መገንዘብ እና ከሀገራዊ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ፣ እና አለማቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር እያሰናሰሉ ጠላትን በሚቀንስ ሁኔታ መንቀሳቀስ የሚችሉ መሪዎች ማለት ነው። እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ እንደ አሜሪካና አውሮፓ ህብረት ያሉ ሀያላን መንግስታት የአማራን ህዝብ ትግል አይደግፉም በሚል በአማራ ሊሂቃን ዘንድ በሰፊው የሚነገረው ሀሳብ ነው።

እነዚህ ሀያላን መንግስታት እስከ ዛሬ ድረስ በአማራ ህዝብ መከራ ላይ፣ ፊታቸውን ማዞራቸው እውነተኛ ቢሆንም ይህን ያደረገው ግን እነሱ የአማራን ህዝብ ትግል ስለማይወዱ ሳይሆን የአማራ ህዝብ ትግል ከእነሱ የፖለቲካ ፍላጎት ጋር ያለውን አወንታዊ መስተጋብር ነቅሶ አውጥቶ በሚፈለገው መጠን የሚያስረዳ መሪ በአማራው ሊሂቃን ዘንድ ስላልተገኘ ነው። በጣም በቀላሉ የአማራ ህዝብ ትግል ከኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ቀጣይነት ጋር የማይጣላ ይልቁንም ኢትዮጵያን የማስቀጠል ሀላፊነት እንዳለበት የሚረዳ እንደሆነ ሳይታክቱ ማስረዳት ቢቻል ሀያላኑ መንግስታት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ያላት የመሪነት ሚና እንዲቀጥል ከመፈለጋቸው ጋር የሚጣጣም ስለሆነ የአማራን ህዝብ ትግል የሚጠሉበት ምክንያት የለም። ምዕራባዊያኑ ሀገራት ይህን በመጠኑም ቢሆን የሚረዱት ቢሆንም የአማራን ህዝብ ትግል ሲደግፉ ያልታዩት አሁን ላይ እየተመዘገበ እንዳለው አይነት ድል የሚያመጣ ጠብሰቅ ያለ ትግል በአማራው በኩል ስላልተደረገ ነበር። በአጭሩ ትግሉን በማስተዋል የሚያደርግ፣ አላማውን የሚያውቅ፣ የተቀናጀ የትግል ስልት የሚከተል ጠንካራ ትግል በአማራው ዘንድ ከተደረገ ምዕራባዊያኑ ትግሉን የማይደግፉበት ምክንያት የለም፤ ምዕራባዊያን የማይደግፉትና ጆሮ የማይሰጡት ጠንካራ ላልመሰላቸው ትግል ብቻ ነው። በተቀረ ከአሸናፊ ጎን የመቆም ችግር የለባቸውም።

የአማራ ህዝብ ትግል አሁን የደረሰበት ደረጃ ደግሞ ታዕምር በሚመስል ሁኔታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ድል እያስመዘገበ ያለ ጠንካራ ትግል ነውና የምዕራባዊያንን ጆሮና ቀልብ እየሳበ ነው።

የሚቀረው ይህን በጎ አጋጣሚ ተጠቅሞ ዲፕሎማሲያዊ ድል ማስመዝገብ የሚችሉ ተደራዳሪ መሪዎችን ከትግሉ ውስጥ ነቅሶ ማውጣት ነው። ይህን ለማሳካት ለአማራው ህዝብ የሚታገሉ ሀይሎች ሁሉ ተሰባስበው መምከር አለባቸው።

4- የአማራን ህዝብ ብዝሃ ፍላጎቶች የሚረዱ ባለፉት ከሰላሳ አመታት ዘለግ ላሉ ጊዜያት የአማራ ህዝብ በከፋ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የህልውና አደጋ ውስጥ በመቆየቱና እነዚህ በደሎች ደግሞ እጅግ በጣም በአስቸኳይ ሊቆሙ እንደሚገባ በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ተደጋግሞ ይነሳሉ። ሆኖም የአማራ ህዝብ ጥያቄዎችና ፍላጎቶች ከህልውና፣ ከሰብዓዊ መብት፣ ከፖለቲካዊ ጥያቄዎች በዘለለ የኢኮኖሚም፣ የማህበራዊም፣ የባህልም፣ የግዛት አንድነትም፣ በውስጠ-ክልል (መልካምድራዊ ፣ ተፈጥሮ ሀብታዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ) ብዛሃነት ሳቢያ የሚነሱ የተለያዩ ፍላጎቶች፣ ተስፋዎችና ስጋቶች አሉ። እነዚህን ሁሉ ፈርጀ ብዙ ፍላጎቶች በጥናት በተደገፈ ሁኔታ አጢኖ፣ በክልሉ ውስጥ የሚገኘው ህዝብ ሁሉ እኩል ተጠቃሚነት፣ ተመሳሳይ ራዕይና የጠበቀ መስተጋብር ኖሮት በአማራነት ህብረት አብሮ የሚቆምበትን መንገድ መተለም ከመሪዎች ይጠበቃል። ከአማራነት ባነሰ የሚደረግ ህብረት ውጤቱ ውድቀትና ተነጥሎ መመታት እንደሆነ የተረዱ፣ ህዝቡንም በዚሁ ቅኝት ማሰባሰብ የሚችሉ መሪዎች ያስፈልጋሉ።

5 - ከግል ስብዕና ግንባታ፣ ከእኔነት (ego centric) ስሜት የራቁ

ላለፉት ረጅም አመታት የአማራን ህዝብ ስቃይ ለማስቆም የተደረጉ ትግሎች ትልቁ ተግዳሮታቸው በአንዳንድ መሪዎቻቸው ዘንድ የሚታየው የኔነት ስሜትና የግል ስብዕናን ከህዝቡ ትግል አላማዎች አስበልጦ ማየት ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በአብን የላይኛው አመራሮች መካከል “ከእኔ የበለጠ አንተ በአማራ ህዝብ ዘንድ ተወደድክ” በሚል ምክንያት የሚደረገው ንትርክ በወለጋ ምድር በአማራ ህዝብ ላይ ሲደረግ ከነበርው የዘር ማጥፋት ወንጀል በልጦ አብዛኛውን የስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ጊዜና ጉልበት ሲወስድ የነበረበት አሳዛኝ ክስተት ነው።

በየጫካው እየታረደ የሚጣልን ህዝብ በደል ለማስቆም የመሪነትን ታሪካዊ ሀላፊነት የተረከበ ቡድን ስለ ራሱ ስም፣ ክብር ወዘተ መጨነቅ ያለበት አልነበረም። ከህዝብ ትግል አስበልጦ ስለ ራስ ዝናና ክብር የሚጨነቅ መሪ የመጀመሪያ ስራው ከጓዶቹ ጋር የስምና የክብር ውድድር ውስጥ መግባት ነው። ለዚህ ራሱ በፈጠረው ውድድር የሚበልጠው ሰው ያለ ከመሰለው ትግሉ ከቆመለት ህዝብ ባላጋራ ጋር መሆኑ ይቀርና ከገዛ ጓዱ ጋር ይሆናል። በዚህም ምክንያት ተደማምጦ፣ ተመካክሮ ለህዝብ ጥቅም የመስራቱ ነገር ውሀ ይበለዋል። በጣም አስቸጋሪው ነገር ደግሞ ዋናው የንትርክ ምክንያት የዝናንና የክብር ውድድር ጉዳይ ሆኖ ሳለ ይሄው ዋና ምክንያት በግልጽ አይነገርም። ስለዚህ ሌላ እውነት ያልሆነ ምክንያት የጠብ መንስኤ ሆኖ ይቀርባል። የተደበቀ በሽታ መድሀኒት የለውምና መፍትሄም አይመጣም። በአብን ሁኔታ ይሄው ምክንያት ተደርጎ የሚቀርበው ሀሰተኛ ምክንያት መንደርተኝነትና ጎጠኝነት ነበር።

በአማራ ማንነቱ እየተሳደደ ላለው ህዝብ ሊታገል የመጣው የመሪዎች ቡድን አንዱ የአማራ መንደር ለሌላኛው ጠላቱ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ በአመራሩ መካከል የማይታረቅ ግን ደግሞ አይረቤ የጠብ ግድግዳ ይገነባል።በዚህም አይቆምም በርካታ ተከታዮችን ሁሉም በየፊናው መንደሩን/ጎጡን ተገን አድርጎ ያሰልፋል። በኋላም የህዝብ ትግል ተረስቶ ትግሉ ራሳቸውን በአጉሊ መነጸር በሚያዩ መሪዎች መካከል ይሆናል። የአማራ ህዝብ በዚህ በመሪዎች ያልተገራ የስብዕና ግንባታና የእኔነት ስሜት ምክንያት ውድ ዋጋ የከፈለ ህዝብ ነው። በዚህ ጽሁፍ መንደርደሪያ ላይ ደግሞ የአማራ ህዝብ ትግል ከዚህ በኋላ ስህተት መድገም የለበትም የሚለው የትግሉ መርሆ እንዲሆን በተጠቀሰው መሰረት አሁን ያለውን የአማራ ህዝብ ትግል የሚመሩ መሪዎች ለህዝብ መቆም የሚቻለው ራስን ከአሸነፉ በኋላ እንደሆነ የተረዱ መሆን አለባቸው።

## 6 - የትግል ስነ-ምግባሮችን የተላበሱ

የአማራ ህዝብ ትግል ስኬት እንዲርቀው ካደረጉ ምክንያቶች አንዱ ትግሉን ለመምራት ወደ ፊት ከመጡ መሪዎች ጠንካራ የትግል ስነ-ምግባር የሚጎድላቸው በርከት ስለሚሉ ነው።

ከእነዚህ የስነ-ምግባር  ጉድለቶች ቀዳሚው የህዝብን ትግል በቁሳዊ ሀብት፣ በሹመት ሽልማት ቅያሬነት አሳልፎ ለአማራ-ጠሉ ስርዓት መሸጥ ነው። ሁለተኛው ብልሹ ስነ-ምግባር መሪ በሆኑ ማግስት የህዝብ እውነተኛ ጥያቄዎችን ችላ በማለት የራስን ህዝብ በሚያቃልሉና በሚያንጓጥጡ ቃላት መወረፍ፣ አልፎ ተርፎ ቆምንልህ ከሚሉት ህዝብ ጋር እልህ መጋባት ነው። በሶስተኝነት ደረጃ የሚመጣው የህዝብን ትግል መምራትን እንደ ኑሮ መደጎሚያ ስራ መመልከት፣ በትግሉ ስም የሚሰበሰብ ሀብትን ለግል ጥቅም ማዋል፣ የጥቅም ቡድንተኝነት በመፍጠር ሀብትን ማባከን፣ ሙስናና ንቅዘትን እንደ ብልጥነት መቁጠር። ሌላው የስነ-ምግባር ችግር ከትግል ጓዶች ጋር ሊመጣ የሚችልን የሀሳብ ልዩነት ክየግል ጠብ አድርጎ በመቁጠር ስም የማጥፋት፣ የመጠላለፍና የጠላትነት ስሜት ማዳበር ነው፣ እነዚህ ችግሮች የአማራ ህዝብ ትግል በእጅጉ የተፈተነባቸውና  በተደጋጋሚ የወደቀባቸው በመሆናቸው አሁን ላይ የሚፈለገው ካለፈው የተማረና ራሱን በስነ ምግባር ያነጸ የመሪዎች ስብስብ ነው።

ከላይ ለመግለጽ የተሞከሩት የሁነኛ መሪ ችሎታ/ባህሪያት በዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ "መግባቢያ" በሚል ርዕስ ስር ከተቀመጡት ሦስት የትግል መርሆዎች አንጻር ነው። እነዚህ የትግል መርሆች ያስፈለጉበት ምክንያት ከወትሮው የድንግርግር መንገድ በተለየ ሁኔታ እየተደረገ ያለውን የአማራ ህዝብ ትግል ወደ ፖለቲካዊ ድል መቀየሩ ምትክ የሌለው ነገር በመሆኑ ለዚህም ሁነኛ መሪዎች መገኘታቸው ምትክ የሌለው መፍትሄ በመሆኑ ነው። የሚፈለገው ሁነኛ የመሪዎች ስብስብ ደግሞ አሁን የአማራ ህዝብ ትግል ያስመዘገባቸውን የድል መንገዶች ሁሉ በፍጥነት ለአማራ ህዝብ ዘላቂ የፖለቲካ ጥቅም ማዋል የሚችል መሆን አለበት። እንዲህ ያሉ ሁነኛ መሪዎች ከማፍራቱ እኩል ጥሩ ተመሪዎች፣ ደጋፊዎችና አባላት የማፍራቱ ጉዳይም እኩል

## ጥሩ መሪዎች እነማን ናቸው

የአማራ ህዝብ/ሊሂቅ በአጠቃላይ ሊባል በሚችል ደረጃ የኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነቱ ጎራ ደጋፊ ብቻ ሳይሆን የጀርባ አጥንት ሆኖ እየኖረ ነው።

በመሆኑም የአማራ ህዝብ በዘውግ ማንነቱ ሳቢያ የመጡበትን ግልጽና ጋህድ አደጋዎች ለመመከት በአማራ ማንነቱ ተደራጅቶ የሚያደርገው ትግል ሁነኛ መሪም ሆነ ተከታይ ሳይኖረው ዘመናት ነጉደዋል፡፡ በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ ብሄርተኝነቱ ጎራ የአማራ ንቅናቄ ጽኑ ተከታይም ሆነ ሁነኛ መሪ እንዳይኖረው ትልቅ ግርዶሽ ጥሎ ቆይቷል፡፡ ሆኖም የአማራ ህዝብ በማንነቱ ምክንያት የተቃጣበትን የህልውና አደጋ በኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነት ጎራ ተሰልፎ መግታት እንደማይችል ሰፊ መግባባት ከተደረሰበት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን መሪም ሆነ ጽኑ ተከታይ የማፍራቱ ነገር ተስፋ ሰጭ እድገት አሳይቷል፡፡

ይህ አበረታች እድገት ግን በቂ አይደለምና ትግሉ ዳር እንዲደርስ ከመሪዎች የሚጠበቀውን ችሎታና ስብዕና ባወሳንበት መንገድ ከተመሪው ተከታይ ህዝብ የሚጠበቀውንም ማየት ያስፈልጋል፡፡ ወደዚህ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ግን “ተመሪ/ተከታይ” የሚለው ቃል የሚያመላክተው የትግሉ አላማ ተከታይነትን እንጅ ግለሰብ መሪዎችን እንዳልሆነ አጽንዖት መስጠት እወዳለሁ፡፡ ይህ ማለት ግለሰብ መሪዎችን የምንከተለው የትግላችን አላማ በትክክል አንግበው እስከሄዱ ድረስ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መሪ ግለሰቦች የመሪነት ማማ ላይ ወጥተው ተከታይ ሊኖራቸው የሚችለው ያነገቡትን አላማ በክብር አጥብቀው እስከያዙ ብቻ ነው፡፡ በተረፈ በህዝብ የትግል አላማ ላይ ቸልተኝነት እያሳዩ ዝም ብላችሁ ተከተሉኝ ማለት ግለሰባዊ አምልኮ አድርጉልኝ ማለት ስለሚሆን ልክ አይሆንም፡፡ ባጭር አነጋገር መሪ እና ተመሪን ህዝብ አያይዞ የሚያቆየው የትግል አላማ ነው፡፡ የትግሉን አላማ ማክበሩ ከሁለት በአንዱ (በመሪም ሆነ በተመሪ) ዘንድ በቸልታ መታየት ከተጀመረ የመሪ እና የተመሪነት ጉዳዩ ጥያቄ ውስጥ ይገባል ማለት ነው፡፡ የመሪ እና የተመሪን ትርጉም እዚህ ላይ እንግታውና ወደ ዋናው ነጥባችን ስንመለስ ከጥሩ መሪ የሚጠበቁ ችሎታና ስብዕናዎችን እንመልከት፡፡

መሪ የሚወጣው ከተመሪው ሰፊ ህዝብ ውስጥ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በመሆኑም አንድ ትግል ጥሩ መሪዎች እንዲያገኝ ጥሩ ተመሪዎች ሊኖሩት ይገባል፡፡

ጥሩ መሪ ለመሆን በመጀመሪያ ጥሩ ተመሪ ሆኖ መቆየት ያስፈልጋል። ጥሩ ተመሪ ምን አይነት ባህሪያት ይኖሩታል የሚለው ወሳኝ ጥያቄ ነውና እሱን ወደ ማየቱ እንለፍ፦

## 1 -ትግሉን አስፈላጊ ያደረጉ ምክንያቶችን (causes) ጠንቅቆ ማወቅ

የአማራ ህዝብ በዘውግ ተደራጅቶ መታገሉን አማራጭ የሌለው መንገድ ያደረጉ ምክንያቶችን ጠንቅቆ መረዳት ዋንኛው ከተመሪው ህዝብ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ይህን ነገር ጠንቅቆ መረዳት ከተለያዩ ጎራዎች የሚመጡ ተግዳሮቶችን ተቋቁሞ ወደ ትግሉ አላማ ብቻ ለመገስገስ ይረዳል፤ ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያ ብሄርተኝነቱና በአማራ ዘውግ ተኮር ንቅናቄ መሀል ያለውን አካሄድ በሚዛናዊ መንገድ ለማስኬድ ይጠቅማል። የአማራን ህዝብ ዘውግ ተኮር ጥያቄዎች ጠንቅቆ ለመረዳት ደግሞ በአማራው ህዝብ ትግል ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሚዲያዎችን ቋሚ በሆነ ፍላጎት መከታተል፣ የሚጻፉ ጽሁፎችን፣ ሰነዶችንና መጸሃፍትን ስራዬ ብሎ ማንበብ ያስፈልጋል። አንድ ትግል ዳር የሚደርሰው በተከታዮች ለትግሉ የመስጠት ጥንካሬ ነው። ለትግል የመስጠት ጥንካሬ የሚመነጨው ደግሞ ስለ ትግሉ ባለ ግንዛቤ ስለሆነ ግንዛቤን ማዳበር ዋነኛው የጥሩ ተከታይነት መለያ ነው። ግንዛቤን ለማዳበር ደግሞ በአማራው ትግል ወዳጆች ብቻ ሳይሆን በተገዳዳሪው አማራ-ጠሉ ጎራ በኩል የሚተላለፉ ሚዲያዎችን፣ የሚጻፉ ጽሁፎችን ሁሉ ተከታትሎ ማንበብ፣ የውይይት መድረኮችን አዘጋጅቶ በይዘታቸው ላይ መነጋገር ሁሉ ያስፈልጋል። ከዚህ አንጻር የአማራ ህዝብ ትግል ደጋፊም ሆነ መሪዎች ያለባቸውን ክፍተት ለመገመት አንዳንድ ነጥቦች እናንሳ። በአማራ ህዝብ ትግል ታሪካዊ ዳራ ውስጥ የዋለልኝ መኮነን ጽሁፍ በስፋት የሚነሳ ጉዳይ ነው። ሆኖም የዋለልኝን ጽሁፍ ጊዜ ወስዶ አንብቦ አሁን ካለው የአማራ ህዝብ ትግል አንጻር ለመቃኘት የሚሞክረው የአማራ ልሂቅ ምን ያህሉ ነው። የዋለልኝ ጽሁፍ በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተጻፈ በመሆኑ የእንግሊዝኛን ቋንቋ አንብቦ መረዳት ለሚያዳግተው የትግሉ ደጋፊ ወደ አማርኛ መልሶ ለማቅረብ የሞከረው የአማራ ሊሂቅ ማን ነው? ( እኔ ራሴ ለአማራ ተማሪዎች ማህበር አባላት ይህን ጽሁፍ ወደ አማርኛ መልሼ ለማቅረብ ቃል ገብቼ የነበረ ቢሆንም ሌላው ሌላው ጉዳይ አላላውስ ስላለኝ እስከ ዛሬ ቃሌን ሳልጠብቅ ቀርቻለሁ።)

የዋለልኝን ጽሁፍ በነሲብ ከመራገም ባለፈ ደርዝ ያለው ውይይት ተደርጎስ ያውቃል? ከዋለልኝ ጽሁፍ ቀጥሎ ለአማራ ህዝብ ትግል አስፈላጊነት ዋነኛ ደወል የሆኑትን የህወሀት የ1968 እና የ1974 አሻሻልኩ ያለው ማኒፌስቶዎች በቅጡ አንብቦ ሙሉ መልዕክታቸውን ማግኘት የቻለው የአማራ ሊሂቅ ምን ያህሉ ነው? በበርካታ ስም የሚደራጁ የአማራ ማህበራትስ እነዚህን የአማራ-ጠሉ ስርዓት አለት በሆኑ ሰነዶች ዙሪያ ለመወያየት ያዘጋጃቸው አውደ-ጥናቶች ኖረው ያውቃሉ? የአማራ ህዝብ አሁን እያለፈበት ያለውን የመከራ ዘመን ያስጀመረው የሽግግር መንግስቱ ቃለ-ጉባኤዎች፣ ሰነዶች አግኝቶ ለማንበብ የሚሞክረው የአማራ ሊሂቅ ምን ያህሉ ነው? የአማራ ህዝብ በወለጋ፣ በቤንሻንጉል፣ በተለያዩ የደቡብ ክልል ቦታዎች የደረሰበትን አሰቃቂ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አስመልክቶ የሚወጡ ሪፖርቶችን ተከታትሎ አንብቦ ለትግሉ ግብዓትነት ለመጠቀም የሚደረገው ጥረትስ ምን ያህል አበረታች ነው? የአማራን ህዝብ የግዛት አንድነት ስጋት በተመለከተ ጥቂት የአማራ ምሁራን የጻፋቸውን እንደ "የወልቃይት ጉዳይ" እና "በረራ፡ ቀዳሚት አዲስ አበባ" ያሉ ደርዝ ያላቸው መጸሀፍት አንብቦ፣ በመጸሓፍቶቹ ዙሪያ የመውያያ መድረኮችን የማዘጋጀቱ ልማድ ምን ያህል አበረታች ነው?

የአማራን ህዝብ ትግል ምክንያቶች (Amhara causes ) ጠብሰቅ አድርጎ ለመረዳት ከፍ ብለው የተጠቀሱትን ልማዶችን ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ልማዶች ያዳበረ ህዝብ ነው ለጽኑ ታጋይነት፣ ለጥሩ ተመሪነት የሚያበቃውን የትግል ስንቅ ሊቋጥር የሚችለው፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን እነዚህን መሰረታዊ የትግል ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ልማዶችን ከማዳበርና ሰፊ ንባብ ከማድረግ ይልቅ ሰበር መረጃዎችን መከታተሉን የበለጠ ጠቃሚ አድርጎ የመውሰድ የተሳሳተ ልምድ ዳብሯል፡፡ ሰበር መረጃዎችን መከታተሉ የሚከፋ ነገር ባይሆንም ትግሉ ያስፈለገባቸውን ታሪካዊና ወቅታዊ የፖለቲካ ሃቆች ለመረዳት ጊዜን መውሰዱ ግን ዋንኛው አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ ዳር የሚደርስ ትግል ማድረግ የሚቻለው መሰረታዊ ፖለቲካዊ ሀቆችን በመረዳት መሆኑ ሊጤን ይገባል፡፡ ጥሩ የትግል አላማ ተከታይ/ደጋፊ መሆን የሚቻለው ስለትግሉ መሰረታዊ ግንዛቤዎችን መጨበጥ ሲቻል ነው፡፡ ስለሚታገለው ትግል መሰረታዊ ሀቆች በቂ ግንዛቤ ያዳበረ ተከታይ በሁኔታዎች መቀያየር የማይናወጥ ጠንካራ የትግል መንፈስ ይኖረዋል፡፡

## 2 - የትግሉን አላማና ግብ መረዳት

በተራ ቁጥር አንድ የተገለጸውን የትግል ምክንያቶች የተረዳ ተከታይ የሚያደርገው ትግል መዳረሻ ግቡ ምን እንደሆነ በውል መረዳት አለበት:: ይህን ለመረዳትም እንዲሁ የተለያዩ ጽሁፎችን ማንበብ፣ በትግሉ ውስጥ የተሻለ መረዳት ያላቸው ሰዎች የሚያዘጋጇቸውን ጽሁፎች፣ የሚቀርቧቸውን ትንታኔዎች በቋሚፍላጎት መከታተል ያስፈልጋል:: ከዚህም በተጨማሪ የአማራ ህዝብን ትግል ለመምራት የሚመጡ መሪዎች እንዲሁም በአማራ ህዝብ ትግል ዙሪያ የሚሰሩ ሚዲያዎች የትግሉን ግብ በተመለከተ ሰፋ ያለ አቅጣጫዎች የሚያሳዩ ስራዎች እንዲሰሩ በመጠየቅ ግንዛቤን ማዳበር ይቻላል:: የትግልን ግብ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነገር በመሆኑ በአማራ ህዝብ ስም የተቋቋሙ የሲቪክ ማህበራትም በዚህ ዙሪያ ሰፊ ስራ መስራት ይኖርባቸዋል:: የተለያዩ የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች ለሰፊው የአማራ ህዝብ የትግሉን አላማ ማስተዋወቅ የሚያስችሉ አውደ ጥናቶች፣ የጥናት ሲንፖዚየሞች ማዘጋጀቱን የስራቸው ዋንኛ አካል አድርገው ቢወስዱ የተሻለ ግንዝቤ መፍጠር ይቻላል:: ሰፊው ደጋፊ/ተከታይ ህዝብ ስለትግሉ አላማ በቂ ግንዛቤ ካዳበረ እያንዳንዱን እንቅስቃሴውን ከትልቁ የትግል ግብ አንጻር ለመቃኘት ይቻላል:: ይህን ማድረግ የቻለ ህዝብ መሪዎቹን የሚለካው ለዚህ ግብ ባላቸው ቁርጠኝነት ይሆናል፤ ትግልና ታጋይን ለይቶ ይመለከታል፤ ታጋይ ቢክድም ወይም ቢያፈገፍግ እንኳን ትግል ሌላ ታጋይ እየተካ እንደሚቀጥል ይገነዘባል:: በመሆኑም ግለሰብን በመውቀስም ሆነ በመርገም ከአስፈላጊው በላይ ጉልበት አያባክንም፣ ትግልም በግለሰቦች ትከሻ ላይ በማንጠልጠል ግለሰቦች ሲወድቁ አብሮ የሚወድቅ የትግል ስልት ከመከተል ይድናል::

## 3 - የትግሉን እውነተኛ መሪዎች ማወቅ

“የትግል እውነተኛ” መሪ የሚለው አባባል ግራ እንዳያጋባ “እውነተኝነት” የሚለካው ስለትግሉ ምክንያትና አላማ ካለን መረዳት አንጻር መሆኑን ግልጽ ማድረግ ያስፈልጋል:: በአሁኑ የአማራ ህዝብ ትግል ሁኔታ ለምሳሌ ሁለት ቡድኖች መሪነቱን ለመውሰድ እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ::

የመጀምሪያው ቡድን የአማራ ህዝብ ትግሉን የሚያደርገው የኢትዮጵያ ብሄርተኝነትን እያሰበና መዳረሻው አድርጎ መሆን አለበት የሚል ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ አማራው አሁን ያለበት ሁኔታ በህይወት የመኖር መብቱን፣ የግዛት አንድነቱን፣ ፖለቲካዊ ተሳትፎውን ጥያቄ ውስጥ የከተተ እጅግ አደገኛ በመሆኑ የአማራ ህዝብ ትግል ቅድሚያ ትኩረት ማድረግ ያለበት ዘውጋዊ ህልውናውና በህይወት የመኖር መብቱን(ሰብዓዊ ክብሩን) ማስጠበቅ ላይ መሆን አለበት፤ የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስትን እጣ-ፈንታ በመወሰኑ ላይ ደግሞ ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር ተነጋግሮ የሚያስተካክለው ነገር መሆን አለበት የሚል ነው።

ከእነዚህ ቡድኖች ውስጥ "እውነተኛው" የአማራ ህዝብ ትግል መሪ ማን ነው የሚለውን ጥያቄ የሚመልሰው ታዲያ ተከታዩ ህዝብ ከሁለቱ ቡድኖች የትግል ምክንያት አረዳድና ግብ አንጻር ያለው አሰላለፍ ነው። ይህም ማለት የአማራ ህዝብ የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስትን የማስቀጠል በለጥያለ ሃላፊነት አለበት ብሎ የሚያስበው የመጀመሪያው ቡድን ደጋፊ ህዝብ እውነተኛ መሪዬ የሚለው የአማራን ህዝብ በህይወት የመኖር መብት ትግል ከኢትዮጵያ ብሄርተኝነት አንጻር እየቃኘ ቀድሞ በተለመደው መንገድ የሚሄደውን የአማራ ልሂቅ ይሆናል ማለት ነው። በአንጻሩ በዚህ ጽሁፍ ላይ በተቀመጠው መሰረት የአማራ ህዝብ ትግል ከቀድሞ በተለየ አዲስ ስልት መሄድ አለበት፣ በመሆኑም ለአማራ ህዝብ በአሁኑ ወቅት አንገብጋቢ ጥያቄ መሆን ያለበት በህይወት የመኖር መብቱን መነጠቅን ጨምሮ በማንነቱ ላይ የተቃጡ አደጋዎችን መቀልበስ ላይ መሆን አለበት የሚለውን ሁለተኛው ቡድን በሚደግፈው ተከታይ ህዝብ እውነተኛ መሪው አማራው ስለ ኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ለማሰብ በመጀመሪያ ራሱ በህይወት መኖር አለበት የሚለውን ቡድን ይሆናል ማለት ነው።

እነዚህ ሁለት ቡድኖች መኖራቸውና በየራሳቸው መንገድ ለመታገል መሞከራቸው ጤናማ ነገር ነው። ጤናማ ያልሆነው የመጀመሪያው ቡድን የሚመሩ መሪዎች የሁለተኛውን ቡድን ስም በማጥፋት፣ በማጣጣልና ጭራሽ እንደዚህ አይነት የፖለቲካ ቡድን የለም እስከ ማለት የሄዱበት አካሄድ ነው።

የሁለተኛው ቡድን ማለትም አማራው ስለኢትዮጵያ ለማሰብ በመጀመሪያ ራሱ በህይወት መኖር አለበትና ለህልውናው ቅድሚያ ሰጥቶ መታገለ አለበት የሚለው ቡድን መሪዎችና ደጋፊዎች በእስር-ቤት የሚገኙ መሆናቸው የሁለቱ ቡድኖች ሀሳብ በተመጣጣኝ ሁኔታ ወደ ሀሳቡ ገበያ እንዳይገባ አድርጓል። እንዲህ ያለው ለሀገራችን ፖለቲካ አዲስ ያልሆነ የመጠላላት፣ የመበላላትና የመጠላለፍና ጥሎ የማለፍ ልክ ያልሆነ አካሄድ ሲያጋጥም በመሀል ገብቶ አካሄዶችን ልክ ማስያዝ ያለበት ተከታዩ ህዝብ ነው። ይህን ማድረግ የሚችለው ደግሞ የትግል አላማውን በውል የተረዳና የሀሳብ ልዩነት ጤናማ መሆኑን የተረዳ ተከታይ ነው። አሁን ባለው የሀገራችን አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታም ሆነ በአማራ ህዝብ ትግል ሁኔታ ተከታዩ ህዝብ ከመሪዎቹ የተሻለ የሀሳብ ልዩነትን ጤናማ ክስተት አድርጎ የመቀበል ትዕግስት ይስተዋልበታል። ይህ በጣም ጥሩ ተስፋ ሰጭ ነገር ሆኖ የበለጠ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ግን ለመጠፋፋት የሚሯሯጠውን የመሪዎች ጎራ ታገስ ተመለስ ማለት ከበሳል ተከታይ ህዝብ የሚጠበቅ ነገር ነው።

## 4 - ተመሪነት አንጻራዊ መሆኑን መረዳት

መሪና ተመሪነት በሰፊው ህዝብና በጥቂት መሪ የተባሉ ግለሰቦች መሀል ብቻ የሚቀር መስተጋብር አይደለም ይልቅስ መሪ በተባሉ ጥቂቶች መሓከልም መሪና ተመሪነት የማይቀር ጉዳይ ነው። ለምሳሌ አንድ የአማራ ድርጅት ያቋቋሙ ሰዎች በአጠቃላይ ከሰፊው ህዝብ አንጻር ሲታዩ መሪ ሊባሉ የሚችሉ ሲሆኑ በድርጅቱ ውስጥ ያሉ አባላት ከድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት አንጻር ሲታዩ ተመሪ የሚባሉ ይሆናሉ። በዚህም አያበቃም እነዚሁ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ደግሞ ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት አንጻር ሲታዩ ተመሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ራሳቸው ከሊቀመንበራቸው አንጻር ሲታዩ ተመሪዎች ሊባሉ ይችላሉ። ይህን መዋቅር ከላይ ወደታች ስናየው ደግሞ መሪነቱ በተጠያቂነት አማካኝነት ተመሪ ለተባሉ አካላት ተጠሪ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ የመሪነትን አንጻራዊነትና የተጠያቂነትን ተዋረድ ተረድቶ፣ በዚሁ መንገድ ለመመራት ሰውን ሳይሆን አላማን ቀዳሚ ጉዳይ አድርጎ ትግል የማስኬዱ ፈለግ ብቻ ነው ወደ ድል-በር የሚያደርሰው።

ወደ ድል-በር ለመድረስ ደግሞ የመሪነትን አንጻራዊነት ተረድቶ በየደረጃው የሚመጣን የመሪና ተመሪነትን ተለዋዋጭ ሁኔታ የመቀበል ትህትና መላበስ ከጥሩ ተመሪ ይጠበቃል። እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ነገር ጥሩ ተመሪ ሳይሆኑ ጥሩ መሪ መሆን የማይቻል መሆኑን ነው።

## 5 - መሪዎችን በማክበርና በግለሰብ አምልኮ መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቅ

ይህን ሚዛናዊነት ለማስጠበቅ የሚረዳው ወሳኙ ነገር ትግልንና ታጋዩን መለየት ብሎም በሁለቱ መካከል ያለ ሚዛን አስጠባቂ ጉዳይ የትግል አላማ እንደሆነ መረዳት ነው። ትግልም ሆነ ታጋይ የሚያስፈልገው አላማን ለማሳካት በመሆኑ ትግልም ሆነ ታጋይ መለካት ያለበት ትግሉ ላነገበው አላማ ባለው ታማኝነት መሆን አለበት። መሪዎች ሰዎች ናቸውና ጠንካራ ጎን እንዳላቸው ሁሉ ደካማ ጎንም ይኖራቸዋል። የመሪዎች ደካማ ጎን ከእኔነት ስሜት (ego) እስከ ክህደት (betrayal) ሊደርስ ይችላል። በእነዚህ ሁለት ደካማ ጎኖች መካከል የሚያርፉ ሌሎች ችግሮችም ይኖራሉ። በዚህ ምክንያት መሪዎች ከዋናው አላማቸው ፈቀቅ ብለው በእርስ በእርስ ሽኩቻ፣ ጠብና ክርክር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። ይህ በአማራ ህዝብ ትግል መሪዎች ላይ ብቻ የሚከሰት ችግር አይደለም ይልቅስ በሁሉም የፖለቲካ ቡድኖች ውስጥ ሊያጋጥም የሚችል ነገር ነው። እንዲህ ያለው ሁኔታ ሲያጋጥም ታዲያ ጥሩ ተመሪ ማድረግ ያለበት አንድን ቡድን ደግፎ ሌላውን ማውገዝ ሳይሆን የተከሰተውን ችግር መሪዎቹ ፊትለፊት መጥተው ለሰፊው ህዝብ እንዲያስረዱ መጠየቅ ነው። በህዝብ ፊት መጥቶ ችግርን ማስረዳት ፍቃደኛ ያልሆኑ መሪዎች የሚኖሩ ከሆነ የችግሩ ፈጣሪ ለመሆናቸው አመላካች ነገር ነው። ምን አልባት ይህን ችግር የፈጠሩ መሪዎች ከዚህ ቀደም በተመሪው ህዝብ ዘንድ የሚወደዱ የነበሩ ከሆኑ ይህን መቀበል ለተመሪው ህዝብ ከባድ ሊሆን ይችላል። ጥንቃቄ መደረግ ያለበት እዚህ ላይ ነው። መሪዎች ለህዝባቸው ቀርበው ችግራቸውን ማስረዳት ካልቻሉና ችግር እየፈጠሩ ከሆነ እየሰሩ ያሉት ከትግሉ አላማ በተቃራኒ ነው ማለት ነው።

እነዚህ መሪዎች ከትግሉ አላማ ፈቀቅ ብለው ጥፋት የሚያመጣ ስራ እየሰሩ በተጨባጭ ካወቅን በኋላም ስለምንወዳቸው ምንም መባል የለባቸውም የሚል አቋም ውስጥ ተመሪው ህዝብ የሚገባ ከሆነ ከትግል አላማ ጋር ካለው ትስስር ይልቅ ከግለሰቦች ጋር ያለን ስሜታዊ ትስስር በልጧል ማለት ነው። በሌላ አባባል ከትግል ይልቅ ታጋይ የበለጠ አስፈላጊ ሆኗል ማለት ነው። የግለሰብ አምልኮ ማለት ይህ አይነት ክስተት ሲፈጠር ነው። የግለሰብ አምልኮ ከተፈጠረ ደግሞ ትግልም ድልም አይገኝም ማለት ነው። የግለሰብ አምልኮን ለማስወገድ ታዲያ አላማን ከሁሉ ነገር ቀዳሚ አድርጎ መውሰድ ቀዳሚው እርምጃ ሲሆን ሰዎች ተሳሳች ፍጡራን እንጅ ፍጹማን አለመሆናቸውን መረዳትም ሌላው አስፈላጊ ነገር ነው። በአጠቃላይ መሪን በማክበርና በማምለክ መካከል ያለውን ሚዛን ለማስጠበቅ አላማን ማዕከለኛ ማድረግ ከስህተት የመዳኛ መንገድ ነው።

በአጠቃላይ ጥሩ ተመሪ ማለት የትግሉን ልጓም እጅ ውስጥ ማስገባት የቻለ ህዝብ ነው። ተመሪው ህዝብ የትግሉን ልጓም እጁ ውስጥ አስገባ ማለት ደግሞ መሪዎቹን በጥብቅ ቁጥጥር ውስጥ አስገብቶ ወደ አምባገነንነት፣ የትግሉን አላማ በራሳቸው የእኔነት ስሜት(ego) ጠልፈው እንዳይጥሉ፣ ለጥቅም አሳልፈው እንዳይሸጡ መጠበቅ ይችላል። ጥሩ ተመሪ ህዝብ መሪዎቹ ከትግል አላማ ፈቀቅ ቢሉ እንኳን ትግሉን ማዳንና መሪን በመሪ መተካት የሚችል ነው። በሌላ አባባል ጥሩ ተመሪ/ተከታይ ያለው ትግል መሪዎቹን ቢያጣ እንኳን ትግሉን የሚያስቀጥል ማለት ነው።

# መቋጫ

ከ1983 ዓ.ም ወዲህ ስልጣን ላይ የወጣው አማራ-ጠሉ ስርዓት በአማራ ህዝብ ላይ ግልጽ የሆኑ ማንነት ተኮር መንግስታዊ ጥቃቶችን ያለማንም ከልካይ ሲፈጽም ኖሯል። አማራ-ጠሉ ስርዓት እንደ መንግስት በዘር ማጥፋት ወንጀል ሊያስጠይቀው የሚችለውን ወንጀል በአማራ ህዝብ ላይ የሚፈጽመውና ሲፈጽም የኖረው በቃለ-ጉባኤ ሳይቀር እያስቀመጠ፣ በግልጽ በአደባባይ የአማራን ህዝብ የሚያሸማቅቁና ለዘር ተኮር ጭፍጨፋ የሚያጋልጡ መልዕክቶችን እያስተላለፈ ነበር። ስርዓቱ ይህን ከባድ ወንጀል ምንም ሳያፍርና ለመደበቅም ሳይሞክር በግልጽ ያደረገ የነበረው ከአማራ ልሂቃን በኩል ይህ ነው የሚባል፣ የተባበረና ስርዓቱን ሊነቀንቅ የሚችል ተቃውሞ ስለማይገጥመው ነበር።ከተቃውሞ ይልቅ በብአዴን በኩል እንደውም ሁለንተናዊ ድጋፉን ያገኝ ነበር።

ሆኖም እጅግ ዘግይቶም ቢሆን የአማራ ህዝብ/ልሂቅ በማንነቱ ምክንያት የመጣበትን አደገኛ የህልውና ስጋት በማንነቱ ተደራጅቶ መመከት እንዳለበት ተረድቶ ትግል ጀምሯል። ይህ ትግል በጣም ዘግይቶ የተጀምረ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ስህተት መስራት የማይፈቀድለት፣ ትግሉን በፍጥነት ግን ደግሞ በትክክለኛነት ማስኬድ ያለበትና የትግል ስልቱን አማራ-ጠሉ ስርዓት ባለመደው አዲስ መንገድ ማስኬድ ያለበት ነው። የአማራ ህዝብ በህይወት የመኖር መብትን ጨምሮ በርካታ ሰብዓዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ መብቶቹን የተነጠቀ ህዝብ በመሆኑ ድል አድርጎ እነዚህን መብቶቹን ከማስመለስ ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም።በአጭር አነጋገር የአማራ ህዝብ ትግል ድል ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ የሌለው ትግል ነው።

የአማራ ህዝብ ትግል በፖለቲካዊ ድል እንዲቋጭ ደግሞ ከተፋፋመው ትግል ውስጥ ሁነኛ መሪዎችን ማውጣት ለነገ የማይባል የቤት ስራ ነው። የአማራ ህዝብ ለረዥም ጊዜ ሁነኛ መሪ አጥቶ በመኖሩ ትግሉን የታገለው የመሪነቱን ቦታ ጭምር እንደ ህዝብ ሸፍኖ ነው። ይህ አማራ የተባለ ሁሉ ሊኮራበት የሚገባ ትልቅ ገድል ነው! ህዝቡ የመሪነቱንም የታጋይነቱንም ቦታ ይዞ በሚገርም ጨዋነት ትግሉን እያስኬደ ያለው የፖለቲካ መሪዎች ቢያገኝ ጠልቶ አይደለም። ነገር ግን የፖለቲካ መሪነቱን ይዞ ህዝቡን በትግል ጎዳና ማስኬድ የነበረበት የአማራ ልሂቅ የኢትዮጵያ ብሄርተኝነት በሚባለው የፖለቲካ ጎራ መመስገን መርጦ በመኖሩ የአማራ ህዝብ በማንነቱ ተደራጅቶ የሚያደገውን ትግል ለመምራት የሚያስችለውን ቁርጠኝነት አልታደልንም።

አሁን ህዝብ ራሱ ትግሉን ተረክቦ የድል ዋዜማ ላይ ይገኛል። ድሉን ዘላቂ ለማድረግ ደግሞ ትግሉን በፖለቲካዊ ድል መቋጨት የሚችል ግንዛቤና ስብዕና ያላቸውን መሪዎች ከትግሉ ውስጥ ፈልቅቆ ማውጣት አስፈላጊ ነገር ነው። የአማራ ህዝብ ትግል መሪዎች ከትግሉ ውስጥ መውጣት አለባቸው ማለት በአማራ ህዝብ እውነተኛ ትግል ወቅት ዳር ይዘው ድምጻቸውን አጥፍተው የነበሩ፣ የአማራን ህዝብ ሲገድሉና ሲያስገድሉ ለነበሩ ካባ ሲያለብሱ የኖሩና የአማራ ህዝብ በየዕለቱ ሲጨፈጨፍ "ዘር ማጥፋት በሚባል ደረጃ እየሞተ አይደለም፣ ለብቻው የደረሰበት ምንም ችግር የለም" ሲሉ የነበሩ አካላት የአማራን ህዝብ ትግል ለመምራት ሊታሰቡ እንኳን አይገባም ማለት ነው። የአማራን ህዝብ ትግል ሊመሩ የሚችሉ መሪዎች ከትግሉ ውስጥ መውጣት አለባቸው ማለት መሪ ሊሆኑ የሚገባቸው በአማራ ህዝብ ክፉ ቀን ከጎኑ ቆመው በሚችሉት ሁሉ ትግሉን የደገፉና በማይናወጥ አቋም የህዝብ ወገንተኝነታቸውን ያስመሰከሩት ብቻ ናቸው ማለት ነው።

የአማራ ህዝብ ትግል ሁነኛ  መሪዎችን ለማውጣት የሚሄድበት መንገድ ትግሉን ለማድረግ ከተደረገው ጥንቃቄ እኩል በጥንቃቄ ሊደረግ የሚገባው ነገር ነው። መሪዎች ለማውጣት የሚደረገው ጉዞ መጀመር ያለበት መሪ መሆን የማይችሉትን በግልጽ ለይቶ በማስቀመጥ መሆን አለበት።

የአማራ ህዝብ ትግል መሪዎች ከትግሉ ውስጥ መውጣት አለባቸው ሲባል ለረዥም ጊዜ ከአማራ ህዝብ ትግል ቅኝት ውጭ የነበሩ፣ ይባስ ብለው የህልውና ትግሉን በዘረኝነት ሲከሱ የነበሩ አሁን ደግሞ ትግሉ ወደ ድል እየገሰገሰ መሆኑን ሲረዱ አለሁበት ለማለት እያንዣበቡ ያሉ አማራ ነኝ ባይ ልሂቃን በመበራከታቸው ነው። እነዚህ ሰዎች ቀድሞ የነበራቸው አቋም ስለሚታወቅ አሁን ብድግ ብለው ስለአማራ ህዝብ ትግል ምክር እንለግስ፣ ታጋይም እንሁን ማለታቸው እውነተኛ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ማወቅ ስለሚያዳግት ለትግሉ ስኬት ሲባል እነዚህን ሰዎች ዳር ማቆየት የጠንቃቃነቱ መንገድ ነው።

ለትግሉ መሪ መሆን የማይችሉትን መለየቱን ያን ያህል የሚያስቸግር ነገር አይደለም። አስቸጋሪው ነገር በትግሉ ውስጥ ከነበሩ የአማራ ልሂቃን ውስጥ የተሻሉ መሪዎችን የማውጣቱ ነገር ነው። በአሁኑ ጊዜ በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ የየራሳቸው ሚና በነበራቸው ልሂቃን መካከል ገንቢ ባልሆነ ሁኔታ እየታየ ያለው የድል ሽሚያ መሪ ማውጣቱን ቀርቶ ትግሉን ራሱን የመጉዳት አቅም ያለው አሳሳቢ ነገር ነው።

በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ሚና በነበራቸው ልሂቃን መካከል እየመጣ ያለው የድል ሽሚያ ዋንኛ ምክንያቱ ድሮም ለአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ትልቅ ፈተና ሆኖ የኖረው በኢትዮጵያ ብሄርተኝነትና በአማራ ህዝብ ትግል መካከል ያለውን መስተጋብር በውል ለይቶ በልኩ በማስኬድ ላይ የተፈጠረ ልዩነት ነው። በዚህ ልዩነት ሳቢያ በአሁኑ ወቅት በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ሁለት ጎራ ተፈጥሯል። የዚህ ጎራ መፈጠር በግልጽ ለህዝብ ይፋ ባለመደረጉ ህዝብ “የትኛው ቡድን ነው የትግሉ መሪ?” በሚለው ነገር ላይ በከፍተኛ ድንግርግር ውስጥ እንዳለ ይታወቃል። አሁን የአማራ ህዝብ የትግል መስመሩን ለይቶ የሚታገልበት እንጅ የሚደናገርበት ስላልሆነ የነዚህን ቡድኖች ማንነት ማሳወቅ ያስፈልጋል።

በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ ካሉ ሁለት ቡድኖች የመጀምሪያው ቡድንበአብዛሃኛው መሪዎቹ እና ደጋፊዎቹ በሀገር ቤት በእስር ላይ የሚገኙ ናቸው።

ይህ ቡድን በውጭ ሀገር ካሉ 'የአማራ ማህበር በአሜሪካ (triple A)፣ የአማራ ማህበራት ፌድሬሽን በሰሜን አሜሪካ( FANA)፣ የአማራ ማህበራት በካናዳና አሜሪካ (CASA) ጋር በጥብቅ ቁርኝት ሲሰራ ሁለት አመታትን ያስቆጠረ ነው። በዚህ ቡድን እሳቤ መሰረት የአማራ ህዝብ የመጀመሪያ ጉዳይ መሆን ያለበት የአማራን ህዝብ በህይወት የመኖር መብት ማስከበርና በሀገሩ ላይ ያለውን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማረጋገጥ መሆን አለበት። የኢትዮጵያን ሀገረ-መንግስት ቀጣይነት በተመለከተ አማራው ከሌሎች የኢትዮጵያ ወንድም/እህት ህዝቦች ጋር ተመካክሮ መግባባት ላይ ለመድረስ በመላ ሀገሪቱ የሚኖረው የአማራ ህዝብ የደህንነት ዋስትና ማግኘት አለበት። በዚህ ቡድን ትንታኔ መሰረት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስትን ቀጣይነትን በተመለከተ ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳዩት በመላ ሀገሪቱ ተበትነው የሚኖሩ የአማራ ተወላጆችንም ሆነ የሌሎችን የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በማክበር መሆን አለበት።

በአማራ ህዝብ ትግል ውስጥ የሚንቀሳቀሰው ሁለተኛው ቡድን በመጀመሪያ የተጠቀሰው ቡድን መሪዎች እስር-ቤት መግባት ተከትሎ ራሱን የገለጠ፣ የመጀመሪያውን ቡድን እንደ ጽንፈኛ የአማራ ብሄርተኛ የሚመለከትና ከሞላ ጎደል ሁሉም በሚባል ደረጃ መሪዎቹ በዲያስፖራ የሚኖሩ ግለሰቦች የሆኑ ነው። በዚህ ቡድን እሳቤ መሰረት የአማራ ህዝብ ትግል የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ቀጣይነት ጉዳይ ከራሱ የህልውና ትግል እኩል ሊሸከመው የሚገባ ጉዳይ ነው ብሎ ያስባል። በዚህም ምክንያት "መነሻዬ አማራነት መድረሻዬ ኢትዮጵያዊነት ነው" ሲል የትግል መስመሩን አስቀምጧል። ይህ ቡድን ዘርዘር አድርጎ ያስቀመጠው የትግል መስመር ትንታኔ ስለሌለ ከዚህ በላይ ስለ ቡድኑ መግልጽ አስቸጋሪ ነው።

ሁለቱ ቡድኖች በአጠቃላይ አላማ ላይ የሰፋ ልዩነት ባይኖራቸውም በአማራ ህዝብ ትግል ትንታኔ ላይ ግን ሰፊ ልዩነት አላቸው። ይሄውም በአጭሩ ሲቀመጥ የመጀመሪያው ቡድን የአማራ ህዝብ ስለ የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግስት ማሰብ የሚችለው በህይወት መኖር ሲችል ስለሆነ መቅደም ያለበት የራሱን ሰብዓዊ ክብር የማስጠበቁ ትግል ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የሀገረ-መንግስት ጥበቃውና በህይወት የመኖር መብት ማስጠበቁ እኩል መሳለጥ አለባቸው የሚል ነው።

በዚህ ልዩነት የተነሳ ሁለተኛው ቡድን የመጀመሪያውን እንደ ጽንፈኛ የአማራ ብሄርተኛ ሲቆጥር የመጀመሪያው ቡድን ደግሞ ሁለተኛው ቡድን ወቅታዊው የአማራ ህዝብ ትግል የደረሰበትን ደረጃ ያለተገነዘበ፣ በቀድሞ ድል-አልቦ ቅኝት ለመጓዝ የሚሞክር ሀይል አድርጎ ይቆጥረዋል።

እነዚህ ሁለት ቡድኖች መኖራቸውን ለአማራ ህዝብ በጊዜ ማሳወቅ ህዝቡ ከገባበት ድንግርግር ወጥቶ ትክክለኛ በመሰለው ቡድን መስመር ተሰልፎ ትግሉ እንዲቀጥል ያደርጋል እንጂ ምንም የሚያመጣው ችግር አይኖርም። "የአማራ ህዝብ ትግል በአዲስ ዘይቤ መደረግ አለበት" ሲባልም እንዲህ ያለውን በጊዜ መገለጥ ያለበት ጉዳይ ለህዝብ ግልጽ ማድረግን ይጨምራል። አብን አሁን ያለበት ደረጃ ላይ የደረሰው በጊዜ ለህዝብ ማሳወቅ የሚገባውን ሀቆች ግልጽ ሳያደርግ በመቆየቱ ነው። የአሁኑ የአማራ ህዝብ ትግል ከቀደሙ ስህተቶቹ የተማረ መሆን ስላለበት ግልጽ  መደረግ ያለበት ጉዳይ ግልጽ መደረጉ መልካም ነው።

የእነዚህ ሁለት ቡድኖች መኖር በአማራ ህዝብ ዘንድ እንደችግር መታየት የለበትም። እንደውም እነዚህ ቡድኖች አፈጣጠራቸውና የትግል ትንታኔያቸውን ለህዝብ ቀርበው አስረድተው፣ ህዝብ ወደ ፈለገው መስመር ገብቶ መታገል እንዲችል ቢደርግ መልካም ነበር። ይህ እንዳይሆን የሚያደርገው የመጀመሪያው ቡድን ሀሳብ አራማጆች ተለቃቅመው አስርቤት መግባታቸው ነው። የሆነው ሆኖ እነዚህ ቡድኖች በመሰላቸው መንገድ ተገዝተው ትግላቸውን ዳር ለማድረስ መሞከራቸው ጤናማ የዴሞክራሲያዊ ትግል አካሄድ ነው። ልክ ያልሆነው በሁለቱ ቡድኖች መካከል መጠላለፍ፣ መካካድ፣ መጠፋፋት መታየት ከጀመረ ነው። ሁለተኛው ቡድን የመጀመሪያውን ቡድን ሀሳብ አራማጆች እስር-ቤት መግባት እንደ መልካም አጋጣሚ ቆጥሮ ራሱን ብቸኛው የአማራ ህዝብ ትግል ሀይል አድርጎ ለማቅረብ እየሄደበት ያለው መንገድ ለትግሉም የማይበጅ ስለሆነ ሊታረም ይገባል። ይህ ቡድን አሁን እየሄደበት ያለው አደገኛ አካሄድ አንድ ሰው የነገረኝን ቁም ነገር አዘል ተረት እንዳስታውስ ያደርገኛል።

ሀገሩ በረሀ በመሆኑ ዝናብ የሚጥለው አመት ሙሉ ሰማይ ተለምኖ ነው። አመት ሙሉ ተናፍቆ የመጣው ዝናብ ሲጥል ታዲያ የደረቀውን መሬት ካራሰ በኋላ በጎድጓዳ ስፍራዎች በጥቂቱ የውሀ ኩሬዎች ይፈጠራሉ። እነዚህ የውሀ ኩሬዎች የተጠሙ ከብቶችን አይንና እግር ይስባሉ። እነዚህ የውሀ ኩሬዎች ተስማምቶ ለመጠጣት ደግሞ የከብትነቱ ተፈጥሮ አያስችልምና እኔ ልቅደም እኔ ልቅደም መራገጥ ተጀመረ። ከብቶቹ ተስማምቶ መጠጣቱ ስላልሆነላቸው ባመጡት መራገጥ ታዲያ ውሀው ወደ ጭቃነት ይቀየርና ማንም ሳይጠጣ እንደ ተጠማ ይቀራል። ይህ ተረት ከአማራ ህዝብ ትግል ጋር የሚዛመደው የአማራ ህዝብ ትግል እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰው ከብዙ አመታት መጠቃትና መዋረድ በኋላ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ትግሉ በበረሀ ላይ በልመና የዘነበውን ዝናብ አይነት ስሜት አለው። ይህን በተዓምር የተገኘ ትግል በብልህ ሰው እሳቤ ማስኬድ ካልተቻለ እንደ በረሃው ሀገር ከብቶቹ በጭቃ መሀል ቆሞ መቅረት ይመጣል።

**መስከረም አበራ**

**ከቃሊቲ እስርቤት**